# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ
## ፫(3)ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ትምህርት ቢሮ የተስማማ

አስማምቶ አዘጋጆች

ብርሃኑ አንዱዓለም ጀንበሬ
ወይኒ አብርሃ ተኽለ

የጥራት ክትትል

ፍሬህይወት አሰፋ ከበደ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለምዓቀፍ የልማት ድርጅት /United States Agency for International Development (USAID)/ በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮና በREAD - TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ሥራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም /General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II/ ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2007 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ትምህርት ቢሮ ነው።

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

ISBN: 978-99944-2-361-3

# ማውጫ


ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች ........ v

1ኛ ሳምንት ........ 1

2ኛ ሳምንት ........ 5

3ኛ ሳምንት ........ 9

4ኛ ሳምንት ........ 13

5ኛ ሳምንት ........ 17

6ኛ ሳምንት ........ 21

7ኛ ሳምንት ........ 25

8ኛ ሳምንት ........ 29

9ኛ ሳምንት ........ 33

10ኛ ሳምንት ........ 37

11ኛ ሳምንት ........ 41

12ኛ ሳምንት ........ 46

13ኛ ሳምንት ........ 50

14ኛ ሳምንት ........ 55

15ኛ ሳምንት ........ 59

16ኛ ሳምንት ........ 64
17ኛ ሳምንት ........ 69
18ኛ ሳምንት ........ 74
19ኛ ሳምንት ........ 78
20ኛ ሳምንት ........ 83
21ኛ ሳምንት ........ 88
22ኛ ሳምንት ........ 93
23ኛ ሳምንት ........ 97
24ኛ ሳምንት ........ 102
25ኛ ሳምንት ........ 107
26ኛ ሳምንት ........ 111
27ኛ ሳምንት ........ 115
28ኛ ሳምንት ........ 119
29ኛ ሳምንት ........ 124
30ኛ ሳምንት ........ 128

# ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የሕጻናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማበልፀግ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርት አካል ነው:: መጽሐፉም ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ሕጻናት ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ የተደረጉ ጥናቶችንና የአማርኛ ቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት ነው::

የዚህ የአፍመፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርትና መርሃትምህርት የተወሰኑ መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው::

1. ሕጻናት እንግዳ ቃላትን ለማንበብና ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር ለመጻፍ፣ የቋንቋው ፊደላት የሚወክሏቸውን ድምፆች መማር ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ የ1ኛና የ2ኛ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርቶችና መርሃትምህርቶች አካል ነው::

2. ሕጻናት በተቻለ መጠን ቃላትን ቀጥሎም ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ አለባቸው፤ እነዚህ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች በተማሯቸው ፊደላት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፤

3. ሕጻናት በፍጥነት፣ በትክክልና ያለችግር እንዲያነቡና ራሳቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመግለጽ እንዲችሉ የማንበብ፣ የመናገርና የመጻፍ በርካታ ተከታታይ ልምምዶች ማድረግ አለባቸው፤

4. ሕጻናት አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የቃላቱንም ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያነቡትን ይረዳሉ፤ ቋንቋቸውንም በንግግርና በጽሑፍ በአግባቡ ይጠቀሙበታል፤

5. ሕጻናቱ ተረቶችን/ታሪኮችንና ሌሎች ጽሑፎችን አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ማዳበር አለባቸው።

## ልጆችዎን በቤት ውስጥ ይርዱ፤

ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት ከሚችሉባቸው አጠቃላይ መንገዶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

1. ለልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን ይንገሯቸው፡፡
2. ልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡
3. ልጆችዎን እርስዎ ስላነበቡላቸው ወይም ስለነገሯቸው ተረቶች/ታሪኮች ወይም ርዕሰጉዳዮች ያሏቸውን አስተያየቶች ለሌሎቻችሁ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው፡፡ ይህም የአንብቦ መረዳትና ጥሩ የመናገር ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል፡፡
4. ለልጆችዎ ራስዎ ወይም ሌሎች ተረት/ታሪክ ያንብቡላቸው፤ ይህም ለልጆቹ የሚያነቡት ጽሑፍ በሌላ ሰው ሲነበብ ምን እንደሚመስል የማዳመጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፤ በራሳቸው ለማንበብም ፍላጎት ያሳድርባቸዋል፡፡ ከልጆቹም ጋር ስላነበባችሁት ጽሑፍ ተወያዩ፡፡
5. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ለደረጃቸው የሚመጥኑ ቀላል ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡ ለማንበብ የሚቸገሩባቸውን ቃላትና ዓርፍተነገሮች እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡
6. ልጆችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

7. ልጆችዎ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ለምሳሌ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞቻቸው ደብዳቤ ወይም በዕለቱ ስለተፈጸመ አንድ ነገር ማስታወሻ በመጻፍ ስሜታቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው።

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

### የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆሙ ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ።

## የማዳመጥ ምንባብ

ይህ ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ ነው።

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- በመምህራቸው የሚነበበውን ተረት/ታሪክ ወይም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ያዳምጣሉ፤
- ርዕሱንና ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ/ ያስባሉ፤

- ስላዳመጡት ምንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በቃላቸው ወይም በጽሑፍ ስለምንባቡ ያላቸውን አስተያየት ለሌሎች ያጋራሉ።

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆች ስለምንባቡ የሚያስታውሱትን እንዲነግሯችሁ ይጠይቁ።
- የሚያስታውሷቸውን በጣም ተፈላጊ ቃላት ወይም ስለምንባቡ ያላቸውን ሀሳብ እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ተረቱን/ታሪኩን መልሰው እንዲተርቱ/እንዲተርኩ ይጠይቁ።



## ማጣመር/መነጠል

ይህ ክፍል ቃላትን በማንበብና ወደተለያዩ ክፍሎች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያግዛቸዋል። በ3ኛ ክፍል ደረጃ ልጆች ፍቺ ስላላቸው የቃላት አሀዶች (ቅጥያዎች) የበለጠ ይማራሉ።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣

- ቃላትን "ማጣመር"፡- ቃላቱ የተመሠረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሀዶች  ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይሷቸዋል።

- ቃላትን "መነጠል"፡ - ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደአነስተኛ አሀዶች ይነጣጥላሉ።

- ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሀዶች (ምዕላዶችን) ይለያሉ፤ ያነባሉ፤ ይረዳሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎን ቃላትን በተለይም በጽሑፉ/ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙትን ረጃጅም ቃላት እንዴት እንደሚያጣምሩና እንደሚነጥሉ እንዲያሳዩዎ ይጠይቁ። ይሄ ለልጆቹ ጠቃሚ ልምምድ ነው።

## ግለንባብ


ይህ ክፍል ሕጻናቱ ዓረፍተነገሮችን፣ አጫጭር ተረቶችን/ታሪኮችን ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን እንዲያነቡ በማድረግ ላይ ያተኩራል። ለንባብ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉት ቃላት በሙሉ ሕጻናቱ ሊያነቧቸው የሚችሉ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በአንብቦ መረዳትም ላይ ያተኩራል።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ግለንባቡን ያነባሉ፤
- ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በግለንባቡ ላይ ይወያያሉ፤
- ስለምንባቡ በደረጃቸው ይጽፋሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- የዕለቱን ግለንባብ ይመልከቱና ልጆቹ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው።
- የቀደሙ ግለንባቦችን ይመልከቱና እንዲያነቡ ይጠይቋቸው።
- ልጆቹ በግለንባቡ ውስጥ ለማንበብ የሚቸገሩባቸው ማናቸውም ቃላት ካሉ ቃላቱን እንዲለዩዋቸውና ዓረፍተነገሩን መልሰው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።
- ልጆችዎ ግለንባቡን መውደድ አለመውዳቸውንና ለምን እንደወደዱት ወይም እንዳልወደዱት ይጠይቋቸው።



## ቃላት

ይህ ክፍል አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም እንዲሁም የቃላቱን ፍቺ ከዐውድ ፈልጎ በማግኘት ስልት (ዘዴ) ላይ ያተኩራል።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ከመምህራቸውና ከሚያዳምጡት ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ፤
- አዳዲስ ቃላትን ከብያኔዎቻቸው ወይም ከሌሎች ቃላት ጋር ያዛምዳሉ፤
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ፤
- ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም ይለማመዳሉ፤
- በዓረፍተነገር ወይም በጽሑፍ ውስጥ ባላቸው ዐውድ መሠረት የቃላትን ፍቺ መወሰን ይለማማዳሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ ስለተማሯቸው ቃላት እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።



## መጻፍ

ይህ ክፍል ቃላትን፣ ዓረፍተነገሮችንና አንቀጾችን በመጻፍ ላይ ያተኩራል።

## በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ቃላትን መጻፍና የቃላቱን ፊደሎች በሥርዓቱ መሠረት መሰደር ይለማመዳሉ፤
- አጫጭር የቃል ጽሕፈትና የፊደል አሰዳደር ሙከራዎች ይወስዳሉ፤
- ሀሳባቸውን ለሌሎች ለማጋራት ዓርፍተነገሮችንና አጫጭር አንቀጾችን ይጽፋሉ።

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፤

- ልጆችዎ የእጅ ጽሕፈታቸውን እንዲያሻሽሉ ፊደሎችንና ቃላትን እንዲገለብጡ ይጠይቋቸው።
- ቃላትን በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ልጆችዎ በሚሳሳቱበት ጊዜ ያበረታቷቸው።
- ልጆችዎ ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት አጫጭር ታሪኮችን/አንቀጾችን በመጻፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የበሽታ መንስኤዎች**

### ቃላት

በ“ሀ” ምድብ ለቀረቡት ቃላት በ“ለ” ምድብ ከቀረቡት ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| “ሀ” | | “ለ” |
|---|---|---|
| 1. ጤነኛ | ሀ. | በአየር የሚተላለፍ የሚያስል በሽታ |
| 2. ጉንፋን | ለ. | በአንድ አካባቢ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃ በሽታ |
| 3. ወረርሽኝ | ሐ. | በምግብና በውሃ መበከል የሚመጣ የሚያስቀምጥ በሽታ |
| 4. ተቅማጥ | መ. | በበሽታ ያልተያዘ |

### ግለንባብ

## አስቴር በሀኪምቤት

አስቴር በምትኖርበት አካባቢ የጉንፋን፣ የወባ፣ የትክትክ፣ የትኩሳትና የራስ ምታት በሽታዎች ተስፋፍተዋል። ከዕለታት አንድ ቀን አስቴር ታመመች፤ ህመሙ ፀናባት። “ምን ባደርግ ይሻላል?” በማለት ጓደኛዋን ጠየቀቻት። ጓደኛዋ፣ “መመርመር አለብሽ” አለቻት።





አስቴር ወደሀኪምቤት ሄዳ ስትመረመር ወባ ስለተገኘባት፣ “እኔ አላምንም!” ብላ ጮኸች። መድሃኒት ታዘዘላት። መድሃኒቱን ስትወስድ ህመሙ ተሻላት።

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
2. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## ማጣመር

ፊደላትን በማጣመር ቃል መስርቱ፡፡

| ፊደላት | ቃል |
|---|---|
| ት - ክ - ት - ክ | ትክትክ |
| ወ - ስ - ፋ - ት | |
| ቁ - ር - ጠ - ት | |
| ኀ - ረ - ቤ - ት | |
| አ - ካ - ባ - ቢ | |
| ወ - ጣ - ቶ - ች | |

## ቃላት

ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ ባዶ ቦታዎቹን አሟሉ፡፡

ወባ ትክትክ

ትኩሳት ወረርሽኝ

ምሣሌ፡- <u>የወባ</u> በሽታ ያንቀጠቅጣል፡፡

1. የ __________ በሽታ ከሰው ወደሰው በትንኝ ይተላለፋል፡፡
2. በ ________ በሽታ የተያዘ ሰው በተከታታይ ይስላል፡፡
3. የወባ በሽታ ከፍተኛ __________ አለው፡፡
4. በሰፈሩ የወባ _________ ስለገባ ብዙ ሰዎች ታመው ተኝተዋል፡፡

## መጻፍ

በአካባቢያችሁ ስለሚዘወተሩ የቤት አሰራሮች ተገቢ ሥርዓተነጥብ በመጠቀም አምስት ዓረፍተነገሮች ፃፉ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የበሽታ መንስኤዎች

ባዳመጣችሁት ምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ::

1. የበቀለና የፀሐይ ሰፈር ምን ዓይነት ነው?
2. በቀለ በሽታዎችን ለማስወገድ ምን ብናደርግ ይሻላል አለ?
3. ማህበረሰቡ “ጎሽ! ተባረኩ!” ያላቸው እነማንን ነው?
4. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

## ማጣመር

በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመጠቀም ባለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃሎች መሥርቱ::

| ፊደላት | ባለሁለት ፊደል ቃል | ባለሦስት ፊደል ቃል |
|---|---|---|
| አ በ ለ ሰ ደ ሳ ባ ከ ጠ ጣ ጨ ጫ | አለ | አበሰ |
| | | |
| | | |
| | | |

## ግለንባብ

### የአካባቢ መበከል



የአንድ ሰፈር ነዋሪዎች በየቦታው ይፀዳዳሉ:: ልጆቻቸው በጉንፋን፣ በተቅማጥ፣ በወስፋትና በቁርጠት ይሰቃያሉ:: መንስዔው የውሃ መበከል እንደሆነ ከባለሙያዎች ተረዱ::

"ምን ብናደርግ ይሻላል?" በማለት የጤና ባለሙያዎችን ጠየቁ:: "አካባቢን ማፅዳት፣ ውሃ አፍልቶ መጠጣትና ንፅህናን መጠበቅ" እንደሆነ ነገሯቸው:: ነዋሪዎች አካባቢያቸውን በማፅዳታቸውና ንፁህ ውሃ በመጠቀማቸው ችግሩ ተቃለለ::

## 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ::

1. ነዋሪዎቹ በየቦታው ምን ያደርጉ ነበር?
2. አካባቢን ማፅዳትና ውሃ አፍልቶ መጠጣት ምን ጥቅም አለው?
3. የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ ሀሳብ በቃላችሁ ተናገሩ::
4. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል ግለፁት::

## ቃላት

ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ዐረፍተነገሮችን መስርቱ::

ምሣሌ:- አበበ <u>ጉንፋን</u> እንዳይዘው ይጠነቀቃል::

1. ጉንፋን 2. ተቅማጥ 3. ወስፋት 4. ቁርጠት 5. ትኩሳት

## መጻፍ

በመማሪያ ክፍላችሁ ያሉትን ነገሮች አስተውላችሁ አምስት አጫጭር ዓረፍተነገሮች ፃፉ::

ምሣሌ:- ሰሌዳው ጥቁር ነው::

2ኛ
ሣምንት

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



### ለህሙማን የሚደረግ እንክብካቤ

## ቃላት

**ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ በምሣሌው መሠረት ባዶ ቦታውን ሙሉ::**


ምሣሌ:- ጥንቃቄ በማድረግ በሽታን መከላከል ይቻላል::

ሀ. ምግብ ለ. መከታተል ሐ. መድኃኒት መ. ንጽሕናን

1. ህሙማን የታዘዘላቸውን _______ ሰዓት ጠብቀው ወሰዱ::
2. የግልና የአካባቢ _______ መጠበቅ ያስፈልጋል::
3. ህጻናት የተመጣጠነ _______ መመገብ አለባቸው::
4. ሀኪሞች በሽተኞችን በየጊዜው _______ ይጠበቅባቸዋል::

## ግለንባብ

### እንክብካቤና ምክር ለከበደ



ከበደ የፋብሪካ ሠራተኛ ነው:: በሥራ ላይ እንዳለ ታመመ:: እያደር በሽታው ፀናበት፤ ከመኝታው መነሳትና መመገብ አቃተው:: "እህ! እህ!" እያለ ያቃስታል::

እህቱ ዘውዴ ወደጤናጣቢያ ወሰደችው:: ባለሙያዎች ህክምናና ተከታታይ እንክብካቤ አደረጉለት:: በመጨረሻም በወንድማዊ አቀራረብ ምክርና ትምህርት ሰጡት:: ከበደ ምክሩንና ትምህርቱን ተቀብሎ ተግባራዊ ስላደረገ ተፈወሰ::

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

1. የከበደ ሥራ ምንድን ነው?
2. ከበደ ወደጤና ጣቢያ ለምን ሄደ?
3. ከበደ የባለሙያ ምክር ተቀብሎ ምን አደረገ?
4. የምንባቡን ዋና ሃሳብ በቃል ግለጹ?

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሣሌ፦ በሥራ = በ — ሥራ
ሙያዎች = ሙያ — ዎች

1. ስለሄደ
2. በልብስ
3. ለበሽታ
4. ስለሰው
5. በሬዎች

### ቃላት

በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ሥር ካሉት ፍቺቻቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. ፀናበት | ሀ. ሀሳብ ማካፈል |
| 2. ያቃስታል | ለ. ዳነ |
| 3. እንክብካቤ | ሐ. እገዛ ማድረግ |
| 4. ተፈወሰ | መ. ቶሎ ቶሎ ይተነፍሳል |
| 5. ማማከር | ሠ. በረታበት |

### መጻፍ

መምህር የሚያነቡላችሁን ባለ20 ቃላት ጽሁፍ አዳምጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በማስገባት ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ለበሽተኞች የሚደረግ እንክብካቤ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. አቶ ከተማና ወይዘሮ ባዩሽን ያመማቸው በሽታ ምንድን ነው?
2. ለወይዘሮ ባዩሽና ለአቶ ከተማ እንክብካቤ ያደረገላቸው ማን ነው?
3. ወይዘሮ ባዩሽና አቶ ከተማ ወጣቶችን በመጨረሻ ምን አሏቸው?
4. የምንባቡን ሃሳብ በአጭሩ ግለፁ?

## ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ቅጥያውን በማጣመር በክፍት ቦታው ሙሉ።

| ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለቅጥያ ቃል |
|---|---|---|
| 1. በሬ | -ዎች | በሬዎች |
| 2. ጫካ | | |
| 3. አውሬ | | |
| 4. መዝጊያ | | |
| 5. ተማሪ | | |
| 6. ዘማሪ | | |

## ግለንባብ

### በጤና መኖር



ጤናማ ለመሆን ምግባችንን በጥንቃቄ መያዝና በአግባቡ መመገብ ያስፈልገናል። የአካባቢና የግል ንጽህና መጠበቅም በጤና ለመኖር ጠቃሚ ነው። ሰዎች በታመሙ ጊዜ ፈጥነው ወደሀኪምቤት መሄድ አለባቸው። በሀኪም ተመርምረው የሚሰጣቸውን መድሃኒት መውሰድ ይኖርባቸዋል። በአጠቃላይ የአካባቢንና የግል ንፅህናን መጠበቅና ሲታመሙ መታከም በጤና ለመኖር ያስችሉናል፤ ጠንካራና አምራች ዜጋ እንድንሆንም ያደርጉናል።

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. አምራች መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?
2. ባጋጣሚ ብንታመም ምን ማድረግ አለብን?
3. በጤና መኖር ያለውን ጥቅም ዘርዝሩ።
4. ጤናችን እንዲጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?

## ማጣመር

በምሣሌው መሠረት በሚከተሉት ቃላት የተለያዩ ቃላትን መስርቱ።

ምሣሌ፡- ሰበረ → አበረ፣ ቀበረ፣ ገበረ

1. ለበሰ 2. ከመረ 3. አጠረ 4. ደረቀ 5. ዘራሽ


## መጻፍ

ጤነኛ ለመሆን ማድረግ የሚገቧችሁን ተግባራት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በስድስት ዐረፍተነገሮች ግለፁ።

ምሣሌ፡- ከመመገቤ በፊት እጄን እታጠባለሁ።

# 3ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን




### ማዳመጥ

ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺቸውን ጻፉ::

ምሳሌ:- ሕክምና → ከበሽታ ለመፈወስ በሐኪምቤት የሚደረግ ክትትል::

ሀ. መከላከል ለ. በሽታ ሐ. ጤናጣቢያ መ. መፀዳጃቤት


### ማጣመር

የሚከተሉትን ፊደሎች በማጣመር ባለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃል መስርቱ::

| የተለያዩ ፊደሎች | ባለሁለት ፊደል ቃል | ባለሶስት ፊደል ቃል |
|---|---|---|
| ል፣ ሿ፣ አ፣ ቋ፣ ተ፣ | አሳ | ልብሷ |
| በ፣ ሳ፣ መ፣ ባ፣ ለ፣ | | |
| ላ፣ ሟ፣ ብ፣ ሷ | | |

### ግለንባብ

#### በሽታን መከላከል



በሽታን ለመከላከል ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? በሽታን ለመከላከል ማድረግ ከሚገቡን ነገሮች አንዱ ውሃን አፍልቶና አጣርቶ መጠቀም ነው:: ይህን በማድረጋችን የልጆቻችን ጤንነት ይጠበቃል:: በነጋ በጠባ ወደጤናጣቢያ አንሄድም፤ ለወጪ አንዳረግም::

የህፃናትን ጤንነት ጠብቀን ካሳደግን በአካልም ሆነ በአዕምሮ ብቁ እናደርጋቸዋለን:: ስለሆነም በሽታን ለመከላከል በጋራ እንሥራ::

## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።**

1. ውሃን በማፍላታችን በውሃ ውስጥ የሚገኙ ውሃ ወለድ በሽታዎች ምን ይሆናሉ?
2. ውሃን አፍልተን ባለመጠጣታችን ምን ምን በሽታዎች ይይዙናል?
3. የምንባቡ መልዕክት ምንድን ነው?

## ቃላት

**ለተሠመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ምሣሌ፡- አልማዝ ለደብተር መግዣ ገንዘብ ወጪ አደረገች።

ወጪ - ልዩ ልዩ ክፍያ

1. ጤናማ ህጻናት በአዕምሮና በአካል ብቁ ናቸው።
2. የግልና የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ ተገቢ ነው።
3. የህጻናት አዕምሮ ብሩህ ነው።
4. ውሃን አፍልቶና አጣርቶ መጠጣት ያስፈልጋል።

## መጻፍ

**የድርጊት ቅደምተከተላቸውን መሠረት በማድረግ አስተካክላችሁ ፃፏቸው።**

ምሣሌ፡- የውሃ ማፍያ ዕቃ ይታጠባል።

1. ውሃው በንፁህ መጠጫ ይጠጣል።
2. ውሃ ይፈላል።
3. የውሃ ማፍያ ዕቃ ይታጠባል።
4. የፈላው ውሃ ይቀዘቀዛል።
5. የሚፈላው ውሃ ከታጠበው ዕቃ ይጨመራል።

# 3ኛ ቀን



## ማዳመጥ

### ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

**የማዳመጥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

1. በሽታን መከላከል ለምን ይጠቅማል?
2. የግል ንፅህና ምን ምንን ያካትታል?
3. በሽታን ለመከላከል የህብረተሰቡ ድርሻ ምን መሆን አለበት?



## ማጣመር

**የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት በማጣመር ጻፉ።**

ምሳሌ፡- <u>እነ-አንተ</u> = <u>እናንተ</u>


| | | |
|---|---|---|
| ሀ. እሱ | ሐ. ከበደ | ሠ. ጀማነሽ |
| ለ. አልማዝ | መ. ሂሩት | |



## ግለንባብ

### ልጆች ተከተቡ!

እማማ በለጡ ዐይነሥውር ናቸው። ማየት ባይችሉም አዕምሯቸው ብሩህ ነው። ሁለት ልጆች አሏቸው። ወቅቱን ጠብቀው ያስከትቧቸው ስለነበር ለበሽታ አልተጋለጡም። ልጆቻቸው ዛሬ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። ሴቷ ሀኪም፣ ወንዱ መምህር ለመሆን በቅተዋል።



እማማ በለጡ ሁልጊዜ የሰፈሩ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያስከትቡ ይመክራሉ። የሰፈሩ የጤናጣቢያ ባለሙያዎች እማማ በለጡን ሁልጊዜ በጥሩ ምሣሌነት ያነሷቸዋል።



## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

1. እማማ በለጡ ወላጆችን ምን ብለው መከሩ?
2. እማማ በለጡን በጥሩ ምሣሌነት የሚያነሷቸው እነማን ናቸው?
3. እማማ በለጡ ልጆቻቸውን በማስከተባቸው ምን ጥቅም አገኙ?
4. የምንባቡን ዋና መልዕክት ባጭሩ ግለፁ።

### ቃላት

በሁለት ቡድን ተደራጁና አንዱ ቡድን ቃሉን ሲጠራ ሌላው ቡድን የቃሉን ፍቺ ይናገር። የቃሉን ፍቺ የተናገረው ቡድን በተራው ቃሉን ሲጠራ ሌላው ቡድን ፍቺውን ይናገራል።

| ቡድን "ሀ" | ቡድን "ለ" |
| --- | --- |
| ክትባት → | በሽታን ለመቋቋም የሚሰጥ መከላከያ |
| በሽታን በመለየት መድሃኒት ማዘዝ ← | ህክምና |

1. ምርመራ
2. ክትባት
3. ጤና ጣቢያ
4. መከላከል
5. ጥንቃቄ

### መጻፍ

"የክትባት ጥቅም" በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮች ያሉት አንድ አንቀፅ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



### የጥሩ ጎረቤቶች ጠቀሜታ

## ቃላት

በቡድን በመወያየት ለቃላቱ ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሣሌ፡- ጎረቤት → ድንበር ተጋርተው ቅርብ ለቅርብ የሚኖሩ ሰዎች።

1. መፈቃቀር 2. ወዳጅነት 3. መጠያየቅ 4. መደጋገፍ

## ግለንባብ

### ጉርብትናና ጥቅሙ



አብሮ መኖር የሰው ልጆችን ማህበራዊ ህይወት ያጠናክራል። ማህበራዊ ህይወት የሚጐለብተው በሰዎች መካከል መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን ሲኖር ነው።

በጥሩ ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች እነዚህን ፀጋዎች ይጋራሉ። የመኖሪያ አካባቢያቸው ምቹና ተናፋቂ ይሆናል። በጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች በበዓላት ቀናት የተጣሉ ወገኖችን ያስታርቃሉ፤ ህሙማንን በጋራ ይጠይቃሉ።

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

1. በጥሩ ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች ምን ምን ነገሮችን ይጋራሉ?
2. ማህበራዊነት የሚጎለብተው በሰዎች መካከል ምን ሲኖር ነው?
3. ጥሩ ጎረቤቶች በበዓላት ቀናት ምን ያደርጋሉ?
4. የጥሩና ጥሩ ያልሆኑ ጎረቤቶችን ልዩነት ዘርዝሩ።

### ማጣመር

የሚከተሉትን ፊደሎች በማጣመር ባለሁለትና ባለሦስት ፊደል ቃላት መሥርቱ።

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ጠ | ዋ | ጣ | ተ | መ | ታ | ማ | በ | ጨ | ባ | ጫ |

| ባለሁለት ፊደል ቃል | ባለሦስት ፊደል ቃል |
|---|---|
| ምሣሌ፡- መጣ | ጨበጠ |

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት በቡድን በመሆን ዐረፍተነገሮችን ስሩ።

ምሣሌ፡- መረዳዳት → ጥሩ ጎረቤቶች በመረዳዳት ይሠራሉ።

1. ወዳጅነት
2. መከባበር
3. መተማመን
4. አብሮ መኖር
5. መቻቻል

### መጻፍ

“የምንወዳቸው ጎረቤቶች” በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮች ያሉት አንድ አንቀፅ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ጉርብትና**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ጥሩ ጉርብትና ምን ምን የነገሱበት ነው?
2. በጎረቤቶች መካከል አለመግባባት ካለ ምን ይከሰታል?
3. በጎረቤቶች መካከል አለመግባባት የሚያመጡ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
4. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ ሀሳብ ባጭሩ በቃላችሁ ግለፁ፡፡

### ማጣመር

"-ኣት" የሚቀጠልባቸውን ቃላት በመምረጥ በምሳሌው መሠረት አጣምሩ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| በሬ | ሰዓት | ካህን | ህጻን |
| ላም | ወንበር | ሴት | ቃል |

| | ዋና ቃል | ዋና ቃልና ቅጥያ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | አባል | አባላት |

### ግለንባብ

## ድር ቢያብር አንበሳ ያስር



ስፖርት ወዳጅነትንና መደጋገፍን ያጠናክራል፡፡ በጉርብትና የሚኖሩት አቶ አስናቀና ወይዘሮ ብርቱካን የሰፈራቸው ወጣቶች መዝናኛ ስለሌላቸው ይቆጩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ለወጣቶቹ ደራሽነታቸውን እንዴት መግለፅ እንዳለባቸው ተወያዩ፡፡

ጎረቤቶቻቸውን በማስተባበር "አዲስ" በሚል ስያሜ የእግር ኳስ ቡድን መሠረቱ፡፡ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንዲሉ፣ የሰፈሩን ነዋሪዎች በማወያየት ገንዘብ አሰባሰቡ፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥም ትጥቅ አሟልተው ለቡድኑ አስረከቡ፡፡ በዚህም የሰፈሩ ነዋሪዎች ተደሰቱ፡፡

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. አቶ አስናቀና ወይዘሮ ብርቱካን በምን ላይ ተወያዩ?
2. የእግር ኳስ ቡድኑን ትጥቅ ማን አሟላው?
3. የሰፈሩን ነዋሪዎች ያስደሰታቸው ምን ነበር?
4. የእግር ኳስ ቡድን ባይቋቋም ኖሮ የሰፈሩ ልጆች ምን ይሆኑ ነበር?

### ቃላት


በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

ሀ. መተጋገዝ
ለ. መከባበር
ሐ. መተማመን
መ. መቻቻል
ሠ. መጣጣም

### መጻፍ

“ተባብሮ የመሥራት ጥቅም” በሚል ርዕስ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም ከአምስት በማይበልጡ ዐረፍተነገሮች አንድ አንቀፅ ጻፉ፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**ጉርብትና**

### ቃላት

በሁለት ቡድን ተደራጁና አንዱ ቡድን ከዚህ በታች ካሉት ቃላት አንዱን ሲጠራ ሌላው ቡድን በቃሉ አጭር ዐረፍተነገር ይመሠርታል:: ዐረፍተነገር የመሠረተው ቡድን ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን በቃሉ ዐረፍተነገር ይመሠርታል:: በዚህ ዓይነት ቃሎች እስኪያልቁ ጨዋታው ይቀጥላል::

ምሣሌ:- ቡድን "ሀ" — ቡድን "ለ"

መደጋገፍ → ርስበርስ የሚደጋገፉ ተማሪዎች ውጤታቸው ከፍ ይላል::

መከባበር ባህላችን ነው:: ← መከባበር

1. መቀራረብ
2. መረዳዳት
3. መተሳሰብ
4. ወዳጅነት

### ግለንባብ

## የጉርብትና መገለጫዎች



ዘር፣ ሃይማኖትና ጾታ ሣይለዩ በአንድ አካባቢ ተቀራርቦ መኖር ለጉርብትና ዋነኛ መገለጫ ነው:: በጎረቤቶች መካከል መከባበር፣ መተማመን፣ መደጋገፍና መተሳሰብ ሊኖር ይገባል:: አንዱ ሌላውን በትህትና ማስተናገድ መከባበር ሲሆን፣ አላስፈላጊ ጥርጣሬ ውስጥ አለመግባት ደግሞ መተማመን ነው:: የችግር ተጋሪ መሆን፣ መደጋገፍና መተሳሰብን ያሣያል:: የተፈጠሩ ችግሮችን ሣያጋንኑ በጋራ መፍትሄ መስጠት የአብሮ ነዋሪዎችን መቻቻል ያመለክታል::

በአጠቃላይ አብሮ መኖር፣ መከባበር፣ መተማመንና መተሳሰብ የመልካም ጉርብትና መገለጫዎች ናቸው::

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. አብሮ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከጉርብትና መገለጫዎች ሦስቱን ግለጹ።
3. መተሳሰብ ማለት ምን ማለት ነው?
4. በጎረቤቶች መካከል ለሚፈጠሩ ችግሮች የጋራ መፍትሔ ባይሰጡ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

## ማጣመር

ዋናውን ቃልና "-ኦች" የሚለውን ቅጥያ በማጣመር ቅጥያ ያለው ቃል መስርቱ።

ምሣሌ፡-

| ተ.ቁ. | ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለ ቅጥያ ቃል |
|---|---|---|---|
| 1 | ቤት | -ኦች | ቤቶች |

2. ልጅ 3. ኮት 4. ልብስ 5. ቀሚስ 6. ሸሚዝ

## ቃላት

በቡድን በመወያየት በምሣሌው መሠረት ዐረፍተነገሮችን መስርቱ።

ምሣሌ፡- መከባበር

ተማሪዎች ርስበርስ <u>መከባበር</u> አለባቸው።

1. መተማመን 2. አብሮ መኖር 3. መቻቻል 4. መተሳሰብ

## መጻፍ

በትምህርትቤታችሁ ግቢ ውስጥ ያያችኋቸውን ነገሮች በአሥር ቃላት ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ምሣሌ፡- መማሪያ ክፍል

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ጉርብትና**

**ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ቤተሰብ ችግር ሲያጋጥመው ቀድሞ የሚደርሰው ማን ነው?
2. የተለያዩ እምነት ተከታዮች በጉርብትና ሲኖሩ በጋራ ምን ያከናውናሉ?
3. ጥሩ ያልሆነ ጉርብትና በምን ይገለጣል?

### መነጠል

**የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ፡፡**

1. ስለሥራ  2. ከቤት  3. በእርሳስ  4. አስመጣ

### ግለንባብ

#### የአንድ ሰፈር ልጆች




አበበችና መላኩ የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው፡፡ አበበች ብዙ ጊዜ አርፍዳ ወደክፍል ትገባለች፡፡ አንድ ቀን መምህሯ አበበችን ማስጠንቀቂያ ሰጧት፡፡

መላኩ አበበችን “ለምን ታረፍጃለሽ?” በማለት ጠየቃት፡፡

አበበች፣ “ሥራ ስለሚበዛብኝ ነው” በማለት መለሰችለት፡፡ መላኩ የአበበችን እናት አነጋገራቸው፡፡ ችግሩ በውይይት ተፈታ፡፡ አበበች ማርፈዷን አቆመች፡፡ አበበችና መላኩ በመረዳዳት ትምህርታቸውን ቀጠሉ፡፡

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. መምህሯ ለአበበች ለምን ማስጠንቀቂያ ሰጧት?
2. መላኩ የአበበችን እናት ስለምን ጉዳይ አነጋገራቸው?
3. አበበች ለምን ወደትምህርትቤት ዘግይታ ትሄዳለች?
4. በምንባቡ ውስጥ እንደችግር የሚጠቀሰው ነገር ምንድን ነው?
5. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

## ቃላት

በቡድን ተደራጁና አንዱ ቡድን ከዚህ በታች ካሉት ቃላት አንዱን ሲጠራ ሌላው ቡድን ተመሳሳይ ፍቺ ያለው ቃል ይናገራል፡፡ ተመሳሳዩን የተናገረው ቡድን በተራው ሌላውን ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን ተመሳሳይ ፍቺ ያለው ቃል ይናገራል፡፡

ምሣሌ፡- ቡድን “ሀ” ቡድን “ለ”

ወዳጅነት → ጓደኝነት

መፈቃቀድ ← መጠያየቅ


1. መደጋገፍ
2. መቀራረብ
3. መከባበር
4. መቻቻል
5. መተማመን
6. መተሳሰብ

## መጻፍ

ወደትምህርትቤት ስትሄዱ በመንገድ ያያችሁትን ነገር በአሥር ቃላት ጻፉና ለመምህራችሁ አሣዩ፡፡

ምሣሌ፡- የቆርቆሮ (የሳር) ቤቶች

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**ማህበራዊ አደረጃጀቶች**

### ቃላት

በቡድን በመወያየት የቃላቱንና የሐረጋቱን ፍቺ ጻፉ::

1. ማህበር
2. ዕድር
3. ዕቁብ
4. አባቶች
5. የሀይማኖት መሪዎች
6. የማህበራት መሪዎች

### ማጣመር

ፊደሎችን በማጣመር ባለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃላትን መስርቱ::

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በ | አ | ጠ | ሰ | ቀ | ጨ | ስ | ወ | መ | ዋ | ም | ጣ | ቃ |

| | ባለሁለት ፊደል ቃል | ባለሶስት ፊደል ቃል |
|---|---|---|
| ምሳሌ:- | ቀጨ | አጠበ |

### ግለንባብ

#### ባህላዊ ተቋማት



ማህበር፣ ዕድርና ዕቁብ ባህላዊ ተቋማት ናቸው:: እነዚህ ተቋማት በሀገራችን ረዥም ዕድሜ አላቸው::

የዕድር አባላት በችግር ጊዜ ፈጥነው ይደርሳሉ:: ወጣቶች፣ ጐልማሶችና አረጋውያን በዕድሮች አማካይነት አካባቢያቸውን ለማልማት በንቃት ይሳተፉባቸዋል::

በጠንካራ የማህበርና የሀይማኖት መሪዎች የሚመሩ ተቋማት የብዙ ዜጎችን ህይወት ቀይረዋል:: አደረጃጀታቸውም ዘመናዊ እየሆነና እየሰፋ መጥቷል::

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

1. ባህላዊ ተቋማት ምን ምን ናቸው?
2. ባህላዊ ተቋማት የሚሳተፉ እነማን ናቸው?
3. ባህላዊ ተቋማት ለህብረተሰቡ የሚሰጡትን ጥቅም ዘርዝሩ።

## ቃላት

ክፍት ቦታውን በተገቢ ቃላት አሟሉ።

ምሣሌ፡- አገሪቱ <u>ለዜጎች</u> ክብር ትሰጣለች።

ሀ. ቡድን   ለ. ጎልማሶች   ሐ. ይደራጃሉ   መ. በንቃት   ሠ. ተቋማት

1. ተማሪዎች የእግር ኳስ ____________ አቋቋሙ።
2. በከተማው ውስጥ የተለያዩ የትምህርት _________ አሉ።
3. በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ____________ ይሳተፋሉ።
4. ሰዎች በተለያዩ ማህበራት ____________።
5. ብርቱካን የ ____________ ትምህርት ትከታተላለች።

## መጻፍ

የጓደኞቻችሁን አለባበስ በመመልከት ያያችሁትን በአምስት ዐረፍተነገሮች የተገነባ አንድ አንቀፅ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሣዩ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### ማህበራዊ አደረጃጀቶች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ሰዎች ለመደራጀት ምን ያስፈልጋቸዋል?
2. የሠፈር ሰዎች ቢጣሉ ማን ያስታርቃቸዋል?
3. የማህበራት መሪዎችን መምረጥ ጥቅሙ ምንድን ነው?
4. በሰፈር አስታራቂዎች ባይኖሩ ምን ችግር ይፈጠራል?

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

1. ወረቀቶች 2. ካህናት 3. ጥሬዎች 4. ኮቶች 5. እነአንተ

### ግለንባብ

#### ተናካሽ ውሻችሁን እሰሩ!

የእትዬ ጫልቱ ውሻ አንድ ቀን የሀጅ ዳውድን ልጅ ነከሳት፤ በዚህ ምክንያት ተጋጩ፡፡ ሀጂ ዳውድ ጉዳዩን ለፖሊስጣቢያ አቀረቡት፡፡

መርማሪ ፖሊስ ጥላዬ፣ “ወይዘሮ ጫልቱ ተናካሽ ውሻችሁን ለምን አታስሩም?” አለ፡፡ እትዬ ጫልቱም፣ “ታስሮ ነበር፤ ድንገት ፈትቶ ነው” አሉ፡፡ ጉዳዩ ወደሽምግልና ተመራ፡፡ የሰፈሩ ሽማግሌዎች አባቶችና እናቶች በአንድነት እትዬ ጫልቱንና ሀጅ ዳውድን በማነጋገር አስታረቋቸው፡፡





# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. የእትዬ ጫልቱ ውሻ ማንን ነከሰ?
2. እትዬ ጫልቱና ሀጅ ዳውድ በምን ተጣሉ?
3. ፖሊሱ እትዬ ጫልቱን ምን አላቸው?
4. የጽሑፉ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር የተገለፁትን ቃላት በ“ለ” ሥር ከተዘረዘሩት ተቃራኒ ቃላት ጋር አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
| --- | --- |
| 1. ተጋጩ | ሀ. ወጣት |
| 2. እርቅ | ለ. መኖር |
| 3. ሽማግሌ | ሐ. ተስማሙ |
| 4. መሞት | መ. መበተን |
| 5. መሰብሰብ | ሠ. ጠብ |
| 6. በቂ | ረ. አነስተኛ |

## መፃፍ

የቡና አፈላል ቅደምተከተልን በአራት ዐረፍተነገሮች ጻፉ።


ምሣሌ፡- ቡና ይለቀማል።

## 7ኛ ሣምንት

### 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ



### ቃላት


የሚከተሉትን ቃላት መርጣችሁ በተገቢው ክፍት ቦታዎች አስገቡ።

| ሁልጊዜ | ጥንታዊ | ማህበራዊ | ባህል |
|---|---|---|---|

1. __________ በቀድሞ ጊዜ የነበረ
2. __________ ልማድ
3. __________ ዘወትር
4. __________ የጋራ

### ግለንባብ

#### ብድር በምድር



ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ወፍ በዛፍ ላይ ተቀምጣ እያለች አንድ ልጅ በወስፈንጥር ያነጣጥርባታል። ይህን የተመለከተች ንብ፣ በርራ ዓይኑን በመንደፍ ወፊቱን አዳነቻት።

"ብድር በምድር" እንዲሉ በሌላ ቀን ንቢቱ ከውሀ ውስጥ ወድቃ ከመስጠም ለመዳን ስትወራጭ ወፊቱ ዓይታ ቅርንጫፍ ቆርጣ በመጣል ከሞት አተረፈቻት ይባላል።

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

1. ወፏን ያዳነቻት ማን ናት?
2. ወፏ ለንቢቱ ምን አደረገችላት?
3. "ብድር በምድር" የሚለው ምሣሌያዊ አነጋገር ምን ማለት ነው?
4. ተረቱን በራሳችሁ አገላለፅ ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።

## መነጠል

በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የሚገኙትን ባለቅጥያ ቃላት ዋናውን ቃል ከቅጥያው ነጥላችሁ ፃፉ።

| ቃል | ዋና-ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|
| 1. ተማሪዎች | ተማሪ | -ዎች |
| 2. ሸሚዞች | | |
| 3. ዘመናት | | |
| 4. አውሬዎች | | |
| 5. ውሻዎች | | |

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዐረፍተነገሮችን ስሩ።

ምሣሌ፡- ውሻ የቤት <u>እንስሳ</u> ነው።

1. ማህበራዊ
2. ተረት
3. ጥንታዊ
4. ባህላዊ
5. ድሮ

## መጻፍ

"ብድር በምድር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና ሀሳብ ከሁለት እስከሦስት በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ባፍ ይጠፉ በለፈለፉ!

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. በሬው በቅናት ስሜት አህያዋን ምን አላት?
2. አርሶአደሩ በሬውንና አህያውን ለምን ወደማሳ ወሰዳቸው?
3. አህያዋ በሬን ምን አለችው?
4. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## ማጣመር

የሚከተሉትን ቅጥያዎች ተጠቅማችሁ በምሣሌው መሠረት ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ።

እነ-፣ -ኦች፣ -ዎች፣ -ኣት

ምሳሌ፡- እሱ → እነ- እሱ = <u>እነእሱ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1. ብርቱካን | 3. ልብስ | 5. ጫማ |
| 2. መዝጊያ | 4. ህጻን | |

## ግለንባብ

### ተረቶቻችን



በጥንት ጊዜ ሰዎች ተረት በመተረት ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር። በዚህም ይዝናኑ፣ ይደሰቱና እርስበርስ ይማማሩ ነበር። ተረት ጾታን፣ ዕድሜን፣ ድሀና ሀብታምን ሣይለይ ሰዎችን ሁሉ እኩል ያዝናናል። የሃይማኖት አባቶች በስብከት፣ አባቶችና እናቶች በጨዋታና በምክራቸው ይገለገሉበታል።

የተረት ባለታሪኮች እንስሳት፣ ሰዎችና ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ተረቶች ሞራልን ያነቃቃሉ። በስድና በግጥም ወይም በሁለቱም ሊቀርቡ ይችላሉ።

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ::

1. የጥንት ሰዎች ምን በማድረግ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ?
2. የተረት ባለታሪኮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
3. ተረቶች ይበልጥ የሚያስደስቱት በየትኛው ዕድሜ ክልል ያሉትን ሰዎች ነው?
4. የተረቱን መልዕክት በአጭሩ ፃፉ::

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዐረፍተነገሮችን ሥሩ::

1. ባለታሪኮች  2. ሀተታ  3. ተረት  4. ጥንት


## መጻፍ

የትምህርትቤታችሁን የኪስሜዳ በመመልከት ያያችሁትን ነገሮች በአሥር ቃላት ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

8ኛ
ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



**የተረት ዋና ዋና ክፍሎችና ተግባሮቻቸው**

### ቃላት


**በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።**

ምሣሌ፡- ተማሪዎች የምንባቡን ይዘት ገለፁ።

1. ተግባር  2. መልዕክት  3. ሥነምግባር  4. ምክር  5. ተግሳፅ

### ግለንባብ

#### አንድነት ኃይል ነው



ልጆችን መምከር፣ መገሰፅና ማስተማር የሚወዱ አንድ አባት ነበሩ። አንድ ቀን ሁሉንም ልጆቻቸውን ሰበሰቡና እያንዳንዳቸው አንዳንድ ብትር እንዲያመጡ አዘዟቸው። ከዚያም “የያዛችሁትን ብትር ስበሩት!” አሏቸው። ሁሉም ሰበሩት። ደገሙና እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ብትሮች እንዲያመጡ አዘዟቸው። ሁሉንም ብትሮች በአንድ ላይ እሠሩና ስበሯቸው!” አሏቸው። ሞከሩና አቃታቸው።

“ልብ በሉ፤ ብቻችሁን ስትሆኑ አቅም አይኖራችሁም። አንድ ላይ ስትሆኑ ግን አንድነት ኃይል ነውና ትጠነክራላችሁ” አሏቸው፣ ይባላል።

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. አባትየው ልጆቹን ምን ማድረግ ይፈልግ ነበር?
2. አባትየው ልጆቹን ምን እንዲፈፅሙ አዘዛቸው?
3. ተረቱን በራሳችሁ አባባል ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።
4. የተረቱ መልዕክት ምንድን ነው?

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ቃል = እናንተ፣ ዋናቃል = አንተ፣ ቅጥያ = እነ-

| | | |
|---|---|---|
| 1. ተማሪዎች | 3. ልጆች | 5. እነሱ |
| 2. ሴቶች | 4. እነአስቴር | 6. ህጻናት |

### ቃላት

በሁለት ቡድን ተደራጁና አንዱ ቡድን ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን ተመሳሳይ ፍቺ ይሰጣል። ፍቺ የሰጠው ቡድን ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን ፍቺ ይናገራል። በዚህ ዓይነት ቃላቱ እስኪያልቁ ጨዋታው ይቀጥላል።

ምሣሌ፡- ቡድን “ሀ” ቡድን “ለ”

መልዕክት → ሀሳብ ማስተላለፍ

ቁጣ ← ተግሳጽ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ይዘት | 3. ሥነምግባር | 5. ማስተማር |
| 2. ተግባር | 4. ምክር | 6. ጀግንነት |

### መጻፍ

የምትወዱትን አንድ አጭር ተረት ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የተረት ዋና ክፍሎችና ተግባሮቻቸው**

በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ::

1. የሰብአዊ ተረቶች ገፀባህሪያት ምንድን ናቸው?
2. አድባሬ ተረት ከሌሎች ተረቶች በምን ይለያሉ?
3. ወላጆች ለልጆቻቸው ተረት ለምን ይተርቱላቸዋል?

### ማጣመር

ከተሰጡት ቅጥያዎች ለዋናው ቃል ተስማሚ የሆኑትን በመምረጥ አጣምሩ::

ስለ-፣ አስ-፣ ከ-፣ ለ-፣ -ኦች፣ -ዎች

1. ቆረጠ
2. ወንበር
3. መኪና
4. ቀሚስ
5. ጫማ

### ግለንባብ

**ከተረቶች ምን እንማራለን?**



ተረቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ጀግንነት፣ ሀቀኝነት፣ የሀገር ፍቅር፣ የነጻነት፣ የብልህነት፣ የታታሪነትና የታማኝነት ስሜትና ባህል እንዲሰፍን ያደርጋሉ:: የአስተማሪነት ባህሪ ስላላቸው በብዛት ተግባር ላይ ይውላሉ::

ተረቶች ሰዎች የትናንቱንና የዛሬውን ብሶት፣ ሀቀኝነት፣ ምሬት እየጠቃቀሱ ነገ የድሎትና የምቾት ጊዜ እንዲሆን የመልካም ራዕይ ነጋሪነት ባህርይ አላቸው::

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ::

1. ተረቶች ለማህበረሰቡ ምን ጥቅም ይሰጣሉ?
2. ተረቶች ምን ዐይነት ባህሪ አላቸው?
3. ተረቶች ምንን ይጠቅሳሉ?
4. መልካም ራዕይ ማለት ምን ማለት ነው?

## ቃላት

ተገቢውን ቃል በመምረጥ ዐረፍተነገሮቹን አሟሉ::

ሀ. ሀቀኛ ለ. ነጻነት ሐ. ታታሪ መ. ታማኝ ሠ. ጀግንነት

1. ወርቁ ስለማይዋሽ ____________ ነው::
2. ለ ____________ የታገሉ አርበኞች ተሸለሙ::
3. አበበ ____________ ሠራተኛ በመሆኑ አለቃው ትወደዋለች::
4. የጥንት አባቶች በ _________ ተዋግተው ጠላትን አሸነፉ::

## መጻፍ

በአቅራቢያችሁ በሚገኙ ገበያዎች ያያችኋቸውን ነገሮች በአምስት አጫጭር ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሣዩ::

# 9ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



ተረት ተረት

### ቃላት

በ"ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ፍቾቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ::

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ | ሀ. በተራችና በአዳማጮች መካከል የሚደረግ የሃሳብ ልውውጥ |
| 2. ተረት ተረት | ለ. ተረት ተናጋሪ |
| 3. የተረት አባት | ሐ. ተረት የሚተርቱ አዛውንት |
| 4. ተራች | መ. የተረት መጀመሪያ |
| 5. ምልልስ | ሠ. ተራቾች ተረቱን ሲያጠናቅቁ የሚናገሩት የተረት መቋጫ ወይም መዝጊያ |

### ግለንባብ

**ተረት**



ተረት፣ ተራችና ታዳሚዎች (አድማጮች) አሉት:: ተረት የሚተርቱ "የተረት አባት" ወይም "ተራች" ይባላሉ:: የተረት አባት ወይም ተራች "ተረትተረት!" ሲሉ፣ አድማጮች "የመሠረት!" በማለት ይቀበላሉ:: በዚህ የምልልስ አግባብ የተረት አባት ወይም ተራች "ተረቴን መልሱ፤ አፌን በዳቦ አብሱ!" በማለት ተረቱን ይደመድማሉ::

ይህ የተረት አቀራረብ ስልት ታዳሚዎችን ያዝናናል:: ተረቱም ጥሩ ሥነምግባርና ጠቃሚ ልምዶችን ያስተምራል::

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የተረት አባት የሚባሉት በየትኛው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ናቸው?
2. "ተረት! ተረት!" በማለት ተረቱን የሚጀምረው ማን ነው?
3. "ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" የሚለው ማን ነው?
4. የተረት ታዳሚዎች ከተረት ምን ጥቅም ያገኛሉ?



## ማጣመር

1. ቃላት ከራሳችሁ ፈልጋችሁ "-ዎች" ወይም "-ኦች" ከሚሉት ቅጥያዎች ጋር በማጣመር ወደብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡

   ምሳሌ፡- እርሳስ → እርሳሶች፣ በሬ → በሬዎች

2. በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ፊደላት በማጣመር ስድስት የተለያዩ ቃላትን መስርቱ፡፡

   ምሣሌ፡- አጠበ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ጠ | ዓ | ጩ | ገ | በ | ነ |
| ረ | ባ | ለ | ቦ | ተ | ፈ | |



## መጻፍ

የመማሪያ ክፍላችሁን ጣሪያ በመመልከት ያያችሁትን ነገር ተገቢ የሆኑ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮችን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ተረት ተረት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::**

1. ዶሮዋ ጫጩቷን የት አገኘቻት?
2. ሲጢጥ ያለው የምን ድምፅ ነበር?
3. የተረት አባት ተረቱን ሲጨርሱ ምን አሉ?

## ማጣመር

**በ"ሀ" ስር የተዘረዘሩትን ቃላት በ "ለ" ሥር ከሰፈሩት ቅጥያዎች ጋር አዛምዱ::**

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| ምሳሌ:- | 1. መጫወቻ → | ሀ. - ኦች |
| | 2. መንገድ | ለ. - ዎች |
| | 3. እሱ | ሐ. - ኣት |
| | 4. ዓመት | መ. እነ- |
| | 5. መኪና | |

## ግለንባብ

### የእናት ምክር



ከዕለታት አንድ ቀን የጭልፊት ልጅ ክንፏ ሳይጠነክር ለመብረር ፈለገች:: ከመብረሯ በፊት እናቷን፣ "ከእንግዲህ መብረር ልጀምር ነውና ምን ትመክሪኛለሽ?" አለቻት:: እናቷም፣ "ሰዎች አንቺን አይተው ጎንበስ ቢሉ፣ እጅ ሊነሱሽ መስሎሽ እንዳትታለይ! ድንጋይ አንስተው ክንፍሽን ሊሰባብሩት ነው" አለቻት ይባላል::

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. መብረር የፈለገችው ማን ናት?
2. ጭልፊቷ ለጫጩቷ ምን ምክር መከረቻት?
3. የእናት ምክር አለመቀበል ምን ጉዳት ያስከትላል?
4. ልጆች ምክር ለምን ያስፈልጋቸዋል?

## ቃላት

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ቃላት ፍቾቻቸውን በፅሁፍ ስጡ።

1. ምክር 2. ጭልፊት 3. ሣይጠነክር 4. ክንፍ

## መጻፍ

“የእናት ምክር” የሚለውን ጽሑፍ በራሳችሁ አባባል በአምስት ዐረፍተነገሮች እንደገና ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 10ኛ ሳምንት

### 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የጊዜ ጥቅም**




### ቃላት

**በ"ሀ" ሥር የቀረቡትን ቃላት በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ::**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መርሃግብር | ሀ. ስኬታማነት |
| 2. ቅደምተከተል | ለ. ማሠራጨት |
| 3. ማቀድ | ሐ. የሥራ ዕቅድ |
| 4. ማከፋፈል | መ. ተከታታይነት |
| 5. ውጤታማነት | ሠ. የሥራ ዝግጅት |

### ግለንባብ

#### ውጤታማ መምህራን



ጊዜን አቅደውና የድርጊት መርሃግብር አዘጋጅተው የሚሠሩ መምህሮች ለተማሪዎቻቸው ተገቢ ዕውቀት ይመግባሉ:: የቀኑን፣ የሳምንቱን፣ የመንፈቀዓመቱን ትምህርት በአግባቡ ከፋፍለው በቅደምተከተል ሥራቸውን ያከናውናሉ::

በዚህ አግባብ ሥራቸውን አቅደው ስለሚሠሩ ተማሪዎች ፍቅርና አክብሮት ይቸሯቸዋል፣ ውጤታማም ይሆናሉ:: በራስ መተማመናቸው ይጨምራል:: ለሌሎች መምህራንም አርአያ ይሆናሉ::

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ።

1. በዕቅድ የሚመሩ መምህሮች ከተማሪዎቻቸው ምን ያገኛሉ?
2. ለተማሪዎች በቂ ዕውቀት የሚሰጡ ምን ዓይነት መምህሮች ናቸው?
3. መምህሮች በራሳቸው የሚተማመኑት ምን ሲያደርጉ ነው?
4. አቅዶ መሥራት የመምህሮች ብቻ ተግባር ይመስላችኋልን? ለምን?

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት በምሣሌው መሠረት ዋናውን ቃል ከቅጥያው ነጥላችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ወሮች → ዋናቃል = ወር፣ ቅጥያ = -ኦች

ስፍራዎች → ዋናቃል = ስፍራ፣ ቅጥያ = -ዎች

1. ተማሪዎች 2. ወንዶች 3. ተራራዎች 4. እነሙሉ 5. አመታት

### ቃላት

ተገቢ ቃላትንና ሐረጋትን መርጣችሁ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ።

ምሣሌ፡- ኅበዝ ተማሪዎች አቅደው ይሠራሉ።

ሀ. ጊዜ፣ ለ. ይቸራሉ፣ ሐ. የድርጊት መርሃግብር፣

መ. መንፈቀዓመት

1. ተማሪዎች የጥናት ____________ ሊኖራቸው ይገባል።
2. የአንደኛው ____________ ፈተና በጥር ወር ይሰጣል።
3. በወጣው ________ መሠረት በመሥራቱ ውጤታማ ሆነ።
4. በጎ አድራጊዎች ለተቸገሩ ሰዎች ገንዘብ ____________።

### መጻፍ

ቤተመጻሕፍት ገብታችሁ በመጻሕፍት መደርደሪያው ላይ ያያችሁትን ነገር ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በአምስት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የጊዜ ጥቅም

በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::

1. ሀብታችን እንዳይባክንና ኢኮኖሚያችን እንዳይቀጭጭ ምን ማድረግ አለብን?
2. ገንዘባችንና ጉልበታችንን በአግባቡ የምንጠቀመው ምን ስናደርግ ነው?
3. ድርጊት በምን ይለካል?

## ማጣመር

ሆሄያትን በማጣመር ባለአራትና ባለአምስት ፊደል ቃላት መስርቱ::

| የተዘበራረቁ ፊደሎች | ባለአራት ፊደል ቃል | ባለአምስት ፊደል ቃል |
|---|---|---|
| ረ አ ነ ጠ ለ ጨ በ<br>ፊ ተ ቀ ባ ገ ጣ | አበጠረ | አነጣጠረ |

## ግለንባብ

### ጎበዙ ደርበው



ደርበው በምርኩዝ የሚሄድ አካል ጉዳተኛ ተማሪ ነው:: ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል:: ከትምህርት በኋላ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች በጊዜ ከፋፍሎ በቅደምተከተል ይሠራል:: በትምህርቱ ውጤታማ ነው::

ሶፊያ የሠፈሩ ልጅ ናት:: ፈተና ሲደርስ አብረው ያጠናሉ:: አንድ ቀን “እንዴት ጉበዝ ልትሆን ቻልክ?” በማለት ጠየቀችው:: ደርበውም፣ “የጊዜ አጠቃቀምን በማወቁ ነው” አላት::

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ደርበው ከትምህርትቤት ሲመለስ ሥራዎችን እንዴት ይሠራል?
2. ሶፊያ ደርበውን ምን ጥያቄ ጠየቀችው?
3. ደርበው ለሶፊያ ጥያቄ ምን ምላሽ ሰጠ?
4. አካል ጉዳተኝነት ጎበዝ ተማሪ ከመሆን የማያግድ መሆኑን የተለያዩ ምሣሌዎችን በመጥቀስ ተናገሩ።

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዐረፍተነገሮችን ሥሩ።

ምሣሌ፡- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም <u>ውጤታማ</u> ያደርጋል።

1. ቅደምተከተል 2. ከፋፍሎ 3. አጠቃቀም 4. ምርኩዝ

### መጻፍ

የመኖሪያ ቤታችሁን አሠራር ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በአምስት ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# 11ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የአቻ ለአቻ ምክር



### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዐረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

1. ጊዜን መወሰን
2. ጥናት
3. መዝናኛ
4. መጠቀም
5. መማር
6. ጨዋታ

### ማጣመር

“-ኦች”ና “-ዎች” የሚሉትን ቅጥያዎች በመጨመር ባለቅጥያ ቃል መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ቅጥያ | ባለቅጥያ ቃል |
|---|---|---|---|
| 1 | ወረቀት | | ወረቀቶች |
| 2 | ሸሚዝ | | |
| 3 | መኪና | -ዎች | |
| 4 | ጠረጴዛ | -ኦች | |
| 5 | ነጠላ | | |
| 6 | ቀሚስ | | |

## ግለንባብ

### ተማሪዎች ጊዜያቸውን የትና እንዴት ያሣልፋሉ?

ተማሪዎች ጊዜያቸውን ለትምህርት፣ ለጥናትና ለመዝናኛ ከፋፍለው መጠቀም ቢችሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ መዘግየትም ሆነ ያለበቂ ምክንያት ከትምህርትቤት መቅረት የትምህርት መርሃግብሩን ይጎዳል፡፡ ሰዓት ማክበር ለራስ ትልቅ ግምት ያሰጣል፡፡

በትርፍ ጊዜ የቤት ሥራ መስራት፣ ማጥናት፣ ቤተመጻሕፍት ገብቶ ማንበብ፣ ከጓደኛ ጋር መጫወትና መዝናናት፣ ወላጅን በሥራ መርዳት "ጎሽ! እደጉ! ተመንደጉ!" ያሰኛል፡፡





## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. የትምህርት መርሃግብሩ የሚጎዳው ምን ሲሆን ነው?
2. ተማሪዎችን "ጎሽ! እደጉ! ተመንደጉ!" የሚያሰኟቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. ጊዜያቸውን ከፋፍለው የማይጠቀሙ ተማሪዎች ምን ችግር ይደርስባቸዋል?
4. ጊዜያችሁን በአግባቡ ለመጠቀም ወላጆችና መምህራን ምን ምን ድጋፎች እንዲሰጧችሁ ትፈልጋላችሁ?

## ቃላት

በ“ሀ“ ረድፍ የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. መርሃግብር | ሀ. ዕድገታችሁ ይጨምር |
| 2. ቤተመጻሕፍት | ለ. ጥሩ ለሠሩ የሚሰጥ አድናቆት |
| 3. ጎሽ | ሐ. የመጻሕፍት ማንበቢያ ክፍል |
| 4. ተመንደጉ | መ. የሥራ ማከናወኛ ዕቅድ |

## መጻፍ

በምሳሌው መሰረት የጨዋታን ጥቅምና ጉዳት ከአምስት በማይበልጡ ዐረፍተነገሮች ፃፉ፡፡

ምሣሌ፡- ጨዋታ ያዝናናል፤ በጊዜ ካልተወሰነ ግን ይጎዳል፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የአቻ ለአቻ ምክር


## መነጠል

በዐረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስሞችና ግሶች ለይታችሁ በማውጣት ፃፉ፡፡

| ተ.ቁ | ዐረፍተነገር | ስም | ግሥ |
|---|---|---|---|
| 1 | አልማዝ ጋቢ ለበሰች፡፡ | አልማዝ፣ ጋቢ | ለበሰች |
| 2 | አገሬ ጫማ አደረገች፡፡ | | |
| 3 | ፈንታሁን ልብስ ሰፋ፡፡ | | |
| 4 | ሙባረክ ኮት ደረበ፡፡ | | |
| 5 | ፋጡማ መኪና ገዛች፡፡ | | |

# ግለንባብ

### ፋጡማ



የቤተመጻሕፍት ኃላፊው አባባ ተስፋዬ "ፋጡማን ታውቂያታለሽ?" አሉ እየሳሉ።

"ፋጡማ ይቺ የአባ ሙሀመድ ልጅ?" አሉ እማማ ዘርፌ!

"አዎን ትክክል ነሽ፤ አውቀሻታል። የተባረከች ልጅ ናት። የትምህርት ቤቱን ሥርዓት አክባሪ ነች። ባለፈው ዓመት በትምህርቷ ከተማሪዎች ብልጫ በማምጣቷ ተሸልማለች። የእኔ ልጆች እንደእሷ ባለመሆናቸው አዝናለሁ" አሉ።

ፋጡማ ስትሄድም ስትሠራም ፈጣን ነች። ጊዜዋን ከፋፍላ ለትምህርት፣ ለጥናት፣ ለጫዋታና ወላጆቿን በሥራ ለመርዳት ትጠቀማለች።

## 4ኛ ቀን

# ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ፋጡማ ምን ዓይነት ተማሪ ናት?
2. ፋጡማ የተሻለ የጊዜ አጠቃቀም እንዲኖራት ማን የሚያግዛት ይመስላችኋል?
3. ፋጡማ የተሸለመችበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. የአባባ ተስፋዬ ልጆች እንደፋጡማ ያልሆኑበት ምክንያት ለምን ይመስላችኋል?

## ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተስማሚውን በመምረጥ ክፍት ቦታውን አሟሉ።

ሀ. የተባረከች　　ሐ. ብልጫ　　ሠ. ተሸለመች

ለ. ሥርዓት　　መ. ቤተመጻሕፍት

1. አገሬ አንደኛ ስለሆነች ________።
2. በሪሁን ________ ገብቶ መጽሐፍ አነበበ።
3. ፋጡማ የነጥብ ________ ስላላት በውድድሩ አሸነፈች።
4. የትምህርትቤት ሕግና ________ ያልተከተለ ተማሪ የምክር አገልግሎት ይሰጠዋል።
5. መስታወት ________ ወጣት በመሆኗ ሰው ይወዳታል።

## መጻፍ


የትምህርትቤታችሁን የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም ደንቦች ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ከአምስት በማይበልጡ ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# 12ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

ጊዜ ወርቅ ነው



### ቃላት

የሚከተሉትን ሐረጋት በቡድን በመወያየት ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡

1. ሥራን መወሰን
2. ቅደምተከተል ማውጣት
3. ጊዜን መከፋፈል
4. በውሣኔ መጽናት
5. ዋዛ ፈዛዛን ማስቀረት

### መነጠል

በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በመነጠል ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ከሰው → ዋናቃል ሰው ቅጥያ ከ-

ሀ. አስመጣ    ለ. አለበሰ    ሐ. ለወንበር    መ. ስለሰበረ    ሠ. በጠረጴዛ

### ግለንባብ

## በጊዜ እንጠቀም

የምናከናውናቸውን ተግባራት ከለየን በአጭር ጊዜ ብዙ ሥራዎችን መፈፀም እንችላለን፡፡ ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የምናከናውነውን ነገር መወሰንና ቅደምተከተል አውጥተን መተግበር ይኖርብናል፡፡ ጊዜን ከፋፍሎና መጥኖ መጠቀም ደግሞ ሌላው ሥራን የማቀላጠፊያ ስልት ስለሆነ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል፡፡

በሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ጊዜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ እንዳያሳልፉ የቅርብ ክትትል ማድረግና መደገፍ ይገባል፡፡

| ዕለት | የተማሪዎች ትርፍ ጊዜ አጠቃቀም መርሃግብር ናሙና | | |
|---|---|---|---|
| | ከ11፡00 - 12፡30 | ከ12፡30-2፡30 | ከ2፡30- 3፡00 |
| ሰኞ | ቤተሰብ በሥራ ማገዝ | ራት መብላት | ማጥናት |

## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

1. ሥራዎችን በወቅቱ ለማከናወን ምን ማድረግ አለብን?
2. ጊዜን ከፋፍሎ መጠቀም ምን ጥቅም ይሰጣል?
3. ከላይ በቀረበው ናሙና መሠረት በሳምንቱ ቀናት ውስጥ የምታከናውኗቸውን ተግባራት አቅዳችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## ቃላት

**በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

ምሣሌ፡- ጊዜን <u>በአግባቡ</u> መጠቀም ይገባል፡፡ በአግባቡ → በትክክል፡፡

1. <u>ተግባራትን</u> በጊዜ ከፋፍሎ መሥራት ይገባል፡፡
2. ሥራችሁን በጊዜ <u>በመመጠን</u> ሥሩ፡፡
3. ወይኒቱ ሥራዋን በወቅቱ <u>አቀላጠፈች፡፡</u>
4. አንድን ሥራ በዘፈቀደ ሣይሆን <u>በስልት</u> መሥራት ይጠቅማል፡፡

## መጻፍ

**መምህር የሚያነቡላችሁን ባለሰላሳ ቃላት ጽሑፍ አዳምጣችሁ በአምስት ደቂቃ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

ጊዜ ወርቅ ነው

## መነጠል

በተሠጠው ምሣሌ መሠረት ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በመነጠል ፃፉ።

ምሣሌ፡- ሀ. ሰበረች → ሰበረ → ዋና ቃል፣ -ች → ቅጥያ

ለ. በሥራ → ሥራ → ዋና ቃል፣ በ- → ቅጥያ

1. ለመሄድ
2. ቤትዋ
3. ልብስሽ
4. ኮትህ
5. በመኪና
6. ከፈረስ

## ግለንባብ

### ጎጂ ልማድ

ወይዘሮ አለምነሽ ጠላና አረቄ ሻጭ ናቸው። መኖሪያ ቤታቸው መንገድ ዳር ስለሆነ የጠላና የአረቄ አተላ፣ የቤት ጥራጊ ፣ የማድቤት አመድ፡ ማንኛውንም ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ መንገድ ዳር አውጥተው ይደፋሉ። በዚህ ምንክያት አካባቢው መጥፎ ሽታ አምጥቷል።




ይህን የተመለከቱት የቀጠናው የልማት አስተባባሪ አቶ ከበደ አንድ ቀን ወይዘሮ አለምነሽን ጠርተው ይህ ሽታ አንቺንም ሆነ የአካባቢውን ማህበረሰብ ይበክላል። በየቦታው ቆሻሻን መጣልና መፀዳዳት ጐጂ ልማድ ነው። ከተማችንን መጠበቅ ያለብን እኛው ነን። ከዚህ ድርጊትሽ ተቆጠቢ ለአሁኑ እኔም ላግዝሽና ቆሻሻውን እናስወግድ በማለት ተባብረው አፀዱ።

ወ/ሮ አለምነሽ በድርጊታቸው ተፀፅተው አቶ ከበደን አመሰገኑ።

## 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በጽሁፍ መልሱ።

1. ወይዘሮ ዓለምነሽ ስራቸው ምንድን ነው?
2. አቶ ከበደ ለወይዘሮ አለምነሽ የሰጡት ምክር ምንድን ነው?
3. ወይዘሮ አለምነሽ ምክሩን ባይቀበሉ ምን ይከሰት ነበር?
4. ወይዘሮ ዓለምነሽ ከጐጂ ድርጊቶቻቸው እንዴት ተቆጠቡ?

## ቃላት

በቡድን በመወያየት በሚከተሉት ቃላት ዐረፍተነገሮችን ስሩ።

ምሣሌ፦ ሻጭ

ወይዘሮ ዓለምነሽ ጠላና አረቄ ሻጭ ናቸው።

1. አተላ    2. ጐጂ    3. ሽታ    4. በከለ


## መጻፍ

በመምህራችሁ የሚነበብላችሁን ጽሁፍ በትክክል በማዳመጥ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የተማሪ ትራፊኮች ኃላፊነታቸውን ተወጡ



### ቃላት

በ“ሀ” ረድፍ የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ::

| “ሀ” | | “ለ” | |
|---|---|---|---|
| 1. | እግረኛ | ሀ. | ግራና ቀኝን ማየት |
| 2. | ማማተር | ለ. | የትራፊክን ህግ ማክበር |
| 3. | ቅድሚያ | ሐ. | በእግሩ የሚጓዝ |
| 4. | ግራን ይዞ መሄድ | መ. | በፊት |

## ማጣመር

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ከቅጥያዎች ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃላት መሥርቱ።

| ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለቅጥያ ቃል |
|---|---|---|
| አሮጌ | -ኣት | አሮጌዎች |
| ሰሌዳ | -ዎች | |
| ዴስክ | -ኦች | |
| አንተ | እነ- | |
| ዘመን | | |
| አስቴር | | |

## ግለንባብ

### የእግረኞች ደህንነት



እግረኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ስለትራፊክ ደህንነት ትምህርት ማግኘት አለባቸው። ትምህርቱም እግረኞች ግራቸውን ይዘው እንዲጓዙ፣ መንገድ ሲያቋርጡ ቆም ብለው ግራና ቀኛቸውን እንዲያማትሩ፣ ለእግረኛ በተፈቀደው ወይም ማቋረጫ ምልክት ባለበት መንገድ ብቻ እንዲያቋርጡ የሚያስገነዝብ ሊሆን ይገባል።


እነዚህን ህግጋት አለማክበር ለከፋ ችግር እንደሚዳርግ ከዚህ በፊት በተጨባጭ የደረሱ አደጋዎችን በምሣሌነት በመጥቀስ ማስተማር ይጠቅማል።

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ።

1. የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ ግራና ቀኝ ማማተር ጥቅሙ ምንድን ነው?
2. እግረኞች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ የትኛውን የመንገድ ጠርዝ ሊይዙ ይገባል?
3. የትራፊክ ሕግ የማያከብሩ መንገደኞች ሊደርሱባቸው የሚችሉትን ጉዳቶች ዘርዝሩ።



## ቃላት

የሚከተሉትን ያልተሟሉ ዐረፍተነገሮች ተገቢውን ቃል/ሐረግ በመምረጥ አሟሉ።

ሀ. ደህንነት ሐ. ማማተር ሠ. እግረኛ

ለ. ሕግ በማክበር መ. ግራን መያዝ

1. መስመር በተሰመረበት የ _________ መንገድ አቋርጡ።
2. የትራፊክ ________ ደህንነታችንን እንጠብቅ።
3. መንገድ ስናቋርጥ ግራ ቀኙን __________ ተገቢ ነው።
4. በመኪና መንገድ ስንጓዝ __________ ያስፈልጋል።
5. የመንገድ __________ ሕግን ማወቅ ከአደጋ ያድናል።



## መጻፍ

የትራፊክ ሕግ አለማክበር በሕይወትና በንብረት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በተመለከተ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ከአምስት በማያንሱ ዐረፍተነገሮች ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የተማሪ ትራፊኮች ኃላፊነታቸውን ተወጡ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. አነሜሮን አቶ ጋሻውን ለምን አስቆሟቸው?
2. እግረኞች ማቋረጥ ያለባቸው የትኛው የትራፊክ መብራት ቀለም ሲበራ ነው?
3. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

### መነጠል


በሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት ዋናውን ቃልና ቅጥያውን በመነጠል ጻፉ።

ምሣሌ፦ ዓመታት → ዓመት -ኣት ወጣቶች → ወጣት -ኦች

1. ፀሐፊዎች
2. ጊደሮች
3. መዝጊያዎች
4. ዘመናት
5. እነአንተ

### ግለንባብ

#### የመኪና አደጋና የእነጥላዬ ውይይት



አንድ ቀን ጥላዬና ጀሚላ አንድ መንገደኛ የመኪና አደጋ ደርሶበት አዩ። የመንገደኛው መጎዳት እነጀሚላን አሳሰባቸው። "ችግሩ እንዳይደገም እንዴት መከላከል እንችላለን?" በማለት ውይይት ጀመሩ።

ጀሚላ፣ "በእግረኛ ላይ የሚደርስውን አደጋ ለመከላከል የእኛ ድርሻ ምን መሆን አለበት?"

ጥላዬ፣ "በመጀመሪያ እኛ የመንገድ ደህንነት ሕግጋትን በደንብ ማወቅ፣ ከዚያም ከቤተሰቦቻችን ጀምሮ ጎረቤቶቻችንና ሌሎች ሰዎችን ማስተማር አለብን" አለ።

ጀሚላ፣ "ሌላስ?" አለች።

ጥላዬ፣ “የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ እንዲያስሩ ለትራፊክ ፖሊሶች ማመልከት” አለ፡፡

ጀሚላ፣ “የእኛ ድርሻ ይህ ብቻ ነው?” አለች፡፡

ጥላዬ፣ “ሌላ ካለ አንቺ ጨምሪ” አላት፡፡

ጀሚላ፣ “የተማሪ ትራፊክ ፖሊስ የመንገድ ህግ ማስከበር” አለች፡፡ ሁለቱም ከውይይቱ በኋላ ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ ተስማሙ፡፡

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ወጣቶቹ በሰፈራቸው ምን አዩ?
2. ጥላዬ “ሌላ ካለ አንቺ ሞክሪ” ሲላት ጀሚላ የሰጠችው ምላሽ ምን ነበር?
3. እግረኛው የመኪና አደጋ የደረሰበት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
4. የምንባቡን ዋና መልዕክት በሁለት ዓረፍተነገሮች ፃፉ፡፡

### ቃላት

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ምሣሌ፡- የመንገድ ደህንነት <u>ሕግጋትን</u> ማወቅ አለብን፡፡

ሕግጋት → ደንብ፣ ሥርዓት

1. ችግሩ እንዳይደገም እንዴት <u>መከላከል</u> እንችላለን?
2. ጥላዬና ጀሚላ ስለመኪና አደጋ ችግር <u>ተወያዩ፡፡</u>
3. ለእግረኛ በተፈቀደው <u>መንገድ</u> አቋርጡ፡፡
4. የተማሪ ትራፊኮች የመንገድ <u>ደህንነት</u> ሕግ አስከበሩ፡፡


### መጻፍ

በሁለት ቡድን ተደራጁ፡፡ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያላችሁ ወንዶች የጥላዬን፣ ሴቶች ደግሞ የጀሚላን ንግግር በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ለሶስት ደቂቃ ያህል በማንበብ አጥኑት፤ ከየቡድኑ አንድ ወንድና አንዲት ሴት የእነጀሚላን ውይይት ያቅርቡ፡፡ ጥሩ ላቀረበው ቡድን ይጨበጨብለታል፡፡

14ኛ
ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



## የትራፊክ ደህንነት

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በቡድን በመወያየት ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሣሌ፡- የትራፊክ ፖሊስ ⟶ የመኪና መንገድ ሥርዓት (ደንብ) አስከባሪ

1. ማቋረጫ
2. አቀበት
3. ህጎች
4. መጎዳት
5. አሽከርካሪ

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

1. ወንበራችን
2. ልብሶችህ
3. ቤትሽ
4. ደብተራቸው
5. እህትህ

### ግለንባብ

## የትራፊክ ፖሊሶች ተግባር



የትራፊክ ፖሊሶች የትራፊክ ደህንነትን ያስከብራሉ። ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት ለአሽከርካሪዎችና ለእግረኞች ስለትራፊክ ደህንነት ይመክራሉ፤ ያስተምራሉ። ደንብና ህግን የሚጥሱ ሲያጋጥሟቸው ይገስጻሉ። ምክርና ትምህርቱን የማይቀበሉትንና የማይፈፅሙትን ለህግ በማቅረብ እንዲታረሙ ያደርጋሉ። የትራፊክ ፖሊሶች የተሽከርካሪዎችና የእግረኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ጥረት ያደርጋሉ። ለአብነት መጥቀስ ቢያስፈልግ የትራፊክ መብራቶችና ልዩ ልዩ የትራፊክ ምልክቶች በተገቢ ቦታቸው እንዲቀመጡ ከሚመለከታቸው

አካላት ጋር ይነጋገራሉ። የትራፊክ ፖሊስ አገልግሎትን ለማስፋትም ተማሪዎችን በሙያው ያሰለጥናሉ። ከጎናቸው በመሆንም አብረው ይሠራሉ።

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ።

1. የትራፊክ ደህንነትን ሕግ የሚያስከብረው ማን ነው?
2. የትራፊክ አደጋ እንዳይከሰት የትራፊክ ፖሊሶች ምን ያደርጋሉ?
3. በምክር በማይመለሱ አሽከርካሪዎች ላይ የሚወሰደው የእርምት እርምጃ ምንድን ነው?
4. የምንባቡን ዋና መልዕክት በሁለት ዓረፍተነገሮች ፃፉ።

### ቃላት

በቡድን በመወያየት ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ማክበር | 2. ደህንነት | 3. መከሰት | 4. ማስተማር |

### መጻፍ

"የተማሪ ትራፊክ ብሆን" በሚል ርዕስ አምስት ዐረፍተነገሮች ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የትራፊክ ደህንነት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

1. የሙያ ሥነምግባር የተላበሱ አሽከርካሪዎች ምን ያደርጋሉ?
2. አሽከርካሪዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች ምን ምን ናቸው?
3. የትራፊክ ሕግ አለማክበር ምን ምን ችግሮች ያስከትላል?

## ማጣመር


ከተሰጡት ቃላት ሌሎች ባለሁለትና ባለሶስት ፊደል ቃላት መሥርቱ::

ምሳሌ:- ልብስ → ባለሁለት ፊደል ልብ ባለሦስት ፊደል = ብስል

1. ሰባበረ
2. ደራረበ
3. አለባበሰ
4. ደጋገመ

## ግለንባብ

### መስቀለኛ መንገድና የትራፊክ ፖሊሶች



በሠፈራችን በሚገኘው መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ብዙ ጊዜ ይከሰት ነበር:: ችግሩን ለመቅረፍ የትራፊክ መጨናነቅ በሚከሰትባቸው ጊዜያት ማለትም ጧት፣ በምሳ ሰዓትና በአሥራሁለት ሰዓት አካባቢ የትራፊክ ፖሊሶች በቋሚነት ተመደቡ::

አንድ ቀን ጧት መንገዶች በመኪናዎች ተጨናንቀው ነበር:: የትራፊክ ፖሊስ ምክትል ሳጅን አህመድ መስቀለኛ መንገዱ መሀል ላይ በመቆም የእለፍና ቁም! የእጅ ምልክት እያሳዩ ተሽከርካሪዎች እንዲስተናገዱ አደረጉ::

ዋና ሳጅን የትነበርሽ ደግሞ የህጻናትን፣ የተማሪዎችንና የአቅመደካማ አዛውንቶችን ደህንነት ለመጠበቅ “ሚጡ፣ ማሙሽ፣ እማማና አባባ” እያሉ እጃቸውን ይዘው በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ እንዲያልፉ ይረዷቸዋል:: የትራፊክ ፖሊሶቹ ይህን በማድረጋቸው ይከሰት የነበረው አደጋ ሊቀንስ ቻለ::

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የትራፊክ መጨናነቅ ባለበት የመኪና አደጋ እንዳይከሰት ምን ተደረገ?
2. ዋና ሳጅን የትነበርሽ ምን በማድረግ እግረኞችን ረዷቸው?
3. የትራፊክ ፖሊሶች በመስቀለኛ መንገድ ላይ ትኩረት ያደረጉት ለምንድን ነው?
4. የመኪና አደጋን ለመቀነስ ከትራፊክ ፖሊሶች በተጨማሪ የእነማን ትብብር ያስፈልጋል?

## ቃላት

በቡድን በመወያየት ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሣሌ፦ መስቀለኛ መንገድ → ሁለት የመኪና መንገዶች የሚተላለፉበት ቦታ

1. ተሽከርካሪ
2. ችግር መቅረፍ
3. አዛውንት
4. የትራፊክ ምልክት

## መጻፍ


ስለትራፊክ ህጎች የምታውቁትን ያህል ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

# 15ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

የመኪና አደጋው ቀነሰ



### ቃላት

በቃላቱ የቢንጎ ጨዋታ በመጫወት ተለማመዱ:: ስለአጨዋወቱ ከመምህራችሁ ተረዱ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መኪና | አደጋ | ሞት | ምልክቶች | ዝግታ | መኪና |
| ዝግታ | መከላከል | መቁሰል | አደጋ | መከላከል | እግረኛ መንገድ |
| ምልክቶች | እግረኛ መንገድ | ማክበር | ማክበር | መቁሰል | ሞት |


### ማጣመር

የተሰመረባቸውን ቃላት ወደብዙ ቁጥር በመለወጥ ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ::

| | የተስተካከሉ ዐረፍተነገሮች |
|---|---|
| ሰው በመኪና መጡ:: | ሰዎች በመኪና መጡ:: |
| ህጻን እንክብካቤ ይፈልጋሉ:: | |
| ልጅ ኳስ ይጫወታሉ:: | |
| ብርቱካን ዛሬ ሄዱ:: | |
| ተማሪ ወደክፍል ገቡ:: | |

# ግለንባብ

## የመኪና አደጋን መከላከል



የመኪና አደጋን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት? አሽከርካሪዎች የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር አለባቸው:: በተለይ የትራፊክ መጨናነቅ ባለበት፣ በከተማ ውስጥና በጠመዝማዛ መንገድ ላይ በዝግታ ማሽከርከር ይገባቸዋል::

በከተሞች ውስጥ ደረጃቸውን የጠበቁ የእግረኛ መንገዶች እንዲሠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል:: በተመሳሳይም የተጎዱና የተበላሹ መንገዶችን ማስተካከል፣ የእግረኛ ማቋረጫ መስመሮችን ማዘጋጀትና መጠቀም አደጋን ይቀንሳል:: እነዚህ ሲሟሉ የመኪና አደጋን በእጅጉ መከላከል ይቻላል::

# 2ኛ ቀን

# ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ::

1. ከአሽከርካሪዎችና ከእግረኞች ምን ይጠበቃል?
2. የተባላሹ የመኪና መንገዶች ምን ጉዳት ያስከትላሉ?
3. በእናንተ አካባቢ ለመኪና አደጋ መከሰት ምክንያት ይሆናሉ የምትሏቸውን ግለፁ::

## ቃላት

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቾቻቸውን ስጡ።

ምሣሌ፡- በከተማ ውስጥ መኪናን በዝግታ መንዳት ተገቢ ነው።

በዝግታ → በቀስታ (አለመፍጠን)

1. የትራፊክ ደህንነትን ሕግ ማክበር ከአደጋ ያድናል።
2. በእግረኛ መንገድ አለመጓዝ ለአደጋ ያጋልጣል።
3. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።

## መጻፍ

የመኪና አደጋን ለመከላከል መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በአምስት ዐረፍተነገሮች ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የመኪና አደጋው ቀነሰ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

1. በመኪና አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው አነማን ናቸው?
2. የመኪና አደጋው በምን ምክንያት ሊከሰት ቻለ?
3. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት ዓርፈተነገሮች ግለጹ።

## መነጠል

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ስሞችንና ግሶችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ::

| ዓረፍተነገር | ስም | ግሥ |
|---|---|---|
| ወይኒቱ ሱሪ ለበሰች:: | ወይኒቱ፣ ሱሪ | ለበሰች |
| ሶፊያ ጋቢ አሠራች:: | | |
| ወንድወሰን ችግኝ ተከለ:: | | |
| ሙባረክ ብር ሰጠኝ:: | | |
| ኤደን ቆብ አደረገች:: | | |

## ግለንባብ

### አሽከርካሪው ለሕግ ቀረበ



በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሽከረክር የነበረ አንድ የከባድ መኪና ሾፌር ፍሬን እምቢ ስላለው ከመስመር ወጥቶ አንድ ቤት ደረመሰ:: በቤቱ ውስጥ የነበሩ አንድ አዛውንት ወዲያው በአደጋው ሞቱ:: አንድ ሌላ ሰው ደግሞ የአካል ጉዳት ደረሰበት:: የአሽከርካሪውን ፊት የመኪናው መስታወት አቆሰለው፤ ንብረት ወደመ:: አካባቢው በጩኸት ተተራመሰ:: አሽከርካሪው ሊሰወር ሲሞክር ተያዘ:: የማይመታው የለም:: አቶ እንግዳ "በህግ ይጠየቃል እንጂ መደብደብ የለበትም" በማለት አሽከርካሪውን ከሞት አዳኑት::

ወይዘሮ ወሰኔ "ምን ብናደርግ ይሻላል?" በማለት አቶ እንግዳን ጠየቁ:: አቶ እንግዳ "ለፖሊስጣቢያ ፈጥነው ይደውሉ" አሏቸው:: ወይዘሮ ወሰኔ ደወሉ፤ የትራፊክ ፖሊሶች መጡ::

አስከሬኑና የተጎዱት ሰዎች ወደሀኪምቤት ተላኩ:: አሽከርካሪው ህክምና ከተደረገለት በኋላ ፖሊስጣቢያ ታሠረ:: ከዚያም ፍርድቤት ቀርቦ ጥፋተኛነቱ በህግ ስለተረጋገጠ ወደማረሚያቤት ተላከ::

## 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ።

1. በፍጥነት ሲሽከረከር የነበረው መኪና ምን ጉዳት አደረሰ?
2. አካባቢው በጩኸት የተተራመሰበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. አቶ እንግዳ ስለአሽከርካሪው ምን አሉ?
4. ከምንባቡ ባለታሪኮች የተሻለ የሕግ ግንዛቤ ያለው ማን ነው?

## ቃላት

በ"ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1. | ንብረት | ሀ. | ተሽከርካሪ |
| 2. | መኪና | ለ. | ጉዳት፣ ችግር |
| 3. | አደጋ | ሐ. | ሀብት |
| 4. | ተሰወረ | መ. | ጠፋ |

## መጻፍ

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ቅደምተከተል በማስተካከል ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ።


ምሣሌ፡- ሄደች ልጅ አጭሯ አሁን

አጭሯ ልጅ አሁን ሄደች።

1. ዛሬ የቀይ ዳማዋ መጣች ወጣት
2. በፍጥነት ባለቆቡ ተራመደ ዲያቆን
3. ታጠናለች ዘወትር ተማሪ ጎበዟ
4. በጣም ጎበዝ እወዳለሁ ተማሪ
5. ተጫዋቹ ደረሰ አዝማሪ በጠዋት

## ግለንባብ

### ጥፋተኞች ተመከሩ



በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ታዋቂ ግለሰብ ነበሩ:: አካል ጉዳተኛ ናቸው:: አካል ጉዳተኛ ቢሆኑም አዕምሯቸው ብሩህ፣ አንደበታቸው ርቱዕ ነው:: "አባ ትልቁ" በመባል ይታወቃሉ:: አጥፊዎችን ይገስፃሉ፤ ይመክራሉ:: አርአያ መሆን የቻሉትን "ጎሽ! በርቱ!" በማለት ያበረታታሉ:: አባ ትልቁ "በሰፈራችን ጥሩ አመለካከትና ሸጋ ባህርይ ያላቸው እንዲሁም ሥርዓት አክባሪና ታዛዥ የሆኑ ወጣቶች ስላሉ እንኮራለን! በሌላ በኩል ትዕቢተኛና ጠብአጫሪ የሆኑ እንዲሁም ሥርቆትና ውሸት የሚወዱ አሉ:: ምን ብናደርግ ይሻላል?" በማለት ከእማማ አስካለና ከአቶ ተሾመ ጋር ተወያዩ::

***"ምንባቡ ከዚህ ቀጥሎ ምን የሚል ይመስላችኋል?"***

እማማ አስካለ "ይህ ጥሩ ሀሳብ ነው:: እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ ሙስና የሚሠሩ፣ አድሎ የሚፈፅሙና ቃላቸውን የማያከብሩ ስላሉ ሊታረሙ ይገባቸዋል!" በማለት ድጋፋቸውን ገለፁ:: አቶ ተሾመ ቀጠሉና "በዚህ ሣምንት ብቻ አንድ ሰው ተደብድቦ ተጎድቷል:: የአንድ አቅመደካማ ሽማግሌ ቤት ተዘርፏል!" አሉ::

አባ ትልቁ "ፖሊስም፣ ቀበሌም እኛ መሆን አለብን:: ጥፋተኞቹ የእኛ ልጆችና ወገኖች ናቸው:: የሚኖሩት ከእኛ ጋር፣ የምናውቃቸው እኛ ነን:: ስለዚህ ሰብሰብ ብለን ከተወያየን በኋላ ነቅሰን እናውጣቸውና እንምከራቸው፤ ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራቸው እናድርግ" አሉ::

በሀሳቡ ሁሉም ተስማሙ፤ ጥፋተኞቹ ተለዩ፤ ተመከሩ:: አጥፊዎቹ በጥፋታቸው ተፀፅተው ህብረተሰቡን ለመካስ ቃል ገቡ::

# 1ኛ ቀን



## ማዳመጥ

### ሰዎችና ሥነምግባራቸው

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የማዳመጥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው ሰዎች ምን ጥቅም ያገኛሉ?
2. ተገቢ ያልሆነ ሥነ-ምግባር ያላቸው ሰዎች በህብረተሰቡ ያላቸው ተቀባይነት እንዴት ነው?
3. ተማሪዎች ጥሩ ሥነምግባር እንዲኖራቸው ኮትኩቶ የማሣደግ ተግባር የማን ይመስላችኋል?
4. የምንባቡን ዋና ሀሳብ ባጭሩ ግለፁ፡፡

## ቃላት

የሚከተሉትን ያልተሟሉ ዐረፍተነገሮች ተገቢ ቃላትን በባዶው ቦታ ላይ በማስገባት አሟሉ፡፡

| መታዘዝ | ሙስና | አመለካከት | ሥርዓት | አርአያ |
|---|---|---|---|---|

ምሳሌ፡- ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው ተማሪዎች ተሸለሙ፡፡

1. መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጥሩ __________ ሊሆኑ ይገባል፡፡

2. ተገቢ ያልሆነ ________ በትምህርት ይቀረፋል፡፡
3. ____________ ማክበር ከተማሪዎች ይጠበቃል፡፡
4. ልጆች ለወላጆቻቸው ____________ አለባቸው፡፡
5. ____________ የሀገርን ዕድገት ያዳክማል፡፡

## መነጠል

**የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፦ ፖሊሶች → ፖሊስ "-ኦች"

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. በሬዎች | 3. ኮቶች | 5. ሴቶች | 7. ፖሊሶች |
| 2. ተማሪዎች | 4. ጋሪዎች | 6. አባቶች | |

## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. "አባ ትልቁ" በመባል የሚታወቁት ሰው ምን ምን ተግባራትን ያከናውናሉ?
2. ጥፋታቸውን አምነው ህብረተሰቡን ለመካስ ቃል የገቡት እነማን ናቸው?
3. የምንባቡ ዋና ባለታሪክ ማን ነው?
4. የምንባቡን ዋና መልእክት በሁለት ዓረፍተነገሮች ግለጹ፡፡

## ቃላት

**በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዐረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡**

1. አጥፊዎች 2. ሥርዓት 3. መጥፎ 4. ጉቦኝነት

## መጻፍ

**"የምወደው መምህሬ" በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡**

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ሰዎችና ሥነምግባራቸው**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

1. አንድ ሰው አርአያ ነው የሚባለው ምን ምን ተግባራትን ሲያከናውን ነው?
2. ተገቢ ያልሆነ ሥነ-ምግባር የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
3. ከዳመጣችሁት ምንባብ የተገነዘባችሁትን ከሁለት እስከሶስት በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ግለፁ?

### ማጣመር

**ራሳችሁ ቃል ፈልጋችሁ "-ኦች" ወይም "-ዎች" ቅጥያዎችን በምሣሌው መሠረት በመጨመር አምስት ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ።**

ምሳሌ፡- ሱሪ → ሱሪ - ዎች → ሱሪዎች

ኮት → ኮት - ኦች → ኮቶች

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።**

1. ወጣቶች የባሕሪ ችግር ስላለባቸው አባ ትልቁ ምን አሉ?
2. እነአባ ትልቁን ለውይይት ያነሳሳቸው ችግር ምንድን ነው?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል ጨርሱ።

## ቃላት

በ"ሀ" ምድብ ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ" ምድብ ከቀረቡት ተመሳሳያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1. | መገሰፅ | ሀ. | ሌብነት |
| 2. | ምሣሌ | ለ. | መቆጣት |
| 3. | ስርቆት | ሐ. | አስቀያሚ |
| 4. | ውሸት | መ. | ቅጥፈት |
| 5. | መጥፎ | ሠ. | አርአያ |

## መጻፍ

ከትምህርት ሰዓት ውጪ ምን ምን ተግባራትን እንደምታከናውኑ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አምስት ዐረፍተነገሮችን ጽፋችሁ አንብቡ።

17ኛ ሣምንት

## ግለንባብ

### የቤተመጻሕፍትና ሌሎች የትምህርትቤት ህጎች




የክፍል ትምህርት ብቻ ለተማሪዎች በቂ አይደለም:: በክፍል ከሚማሩት ትምህርት በተጨማሪ ሌሎች መፃሕፍትን በማንበብ ዕውቀታቸውን ማስፋት ይኖርባቸዋል:: ለዚህም ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው ወደቤተመጻሕፍት በመግባት ማንበብ ይጠበቅባቸዋል:: ወደቤተመጻሕፍት ሲሄዱም ደንቡን ማወቅና ማክበር ተገቢ ነው:: ሊከበሩ ከሚገባቸው የቤተመጻሕፍት ህጎች መካከል ግንባር ቀደሞቹ ከእስክሪቢቶና ከማስታወሻ ደብተር በስተቀር ሌላ ነገር አለመያዝ፣ ሲያነቡ ድምፅ አለማሰማት፣ ከሌሎች ጋር አለማውራት፣ ዕርዳታ ሲፈልጉ የቤተመጻሕፍቱን ሠራተኞች ቀስ ብሎ መጠየቅ ናቸው::

✶✶✶"ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የቤተመፃሕፍት ህጎች ተናገሩ::"✶✶✶

በሌላም በኩል ተማሪዎች በክፍል አለቃቸው አማካኝነት የክፍል ፅዳት ፕሮግራም ያወጣሉ:: በወጣው ፕሮግራም መሠረት በየቀኑ ሁለት ሁለት ተማሪዎች ክፍል ያፀዳሉ:: ቆሻሻውን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ ይጨምራሉ:: ክፍላቸውን ሁልጊዜ በንፅህና ስለሚይዙ ጤንነታቸው የተጠበቀ ነው::

ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፋቸውን በመሸፈን በንፅህና መያዝ ይገባቸዋል:: በዓመቱ መጨረሻም የመጻሕፍቱ ንፅህና እንደተጠበቀ ለትምህርትቤቱ ይመለሳሉ:: ቀጣዮቹ ተማሪዎችም በንፅህና ጠብቀው ይጠቀሙባቸዋል::

በተጨማሪም ተማሪዎች የትምህርትቤቱን ማህበረሰብ፣ መምህራንና ታላላቆቻቸውን ማክበር ይገባቸዋል:: መሰል ጓደኞቻቸውንም ማክበርና መውደድ ያስፈልጋል:: ይህን ሲያደርጉ እነሱም ይወደዳሉ፤ ይከበራሉ::

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



### የትምህርትቤት ሕግና ደንብ አከባበር

## ቃላት

1. በ"ሀ" ረድፍ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጎች በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ፍቺዎች ጋር በቀስት አገናኙ።

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1. | ደንብ | ሀ. | ለደንብና ለሥርዓት ተገዢ መሆን |
| 2. | ሰንደቅዓላማ | ለ. | ለአስተማሪዎች ቅንና ትሁት መሆን |
| 3. | ትምህርትቤት | ሐ. | በጊዜው መገኘት |
| 4. | ሰዓት ማክበር | መ. | ባለቀለማት የሀገሮች መለያ |
| 5. | ሕግ ማክበር | ሠ. | መማሪያ ተቋም |
| 6. | መምህራንን ማክበር | ረ. | ሕግ፣ ሥርዓት |

2. ተስማሚ ስሞችንና ግሶችን በመምረጥ በተገቢው ቦታ አስገቡ።

| ሥምና ግሶች | ተ.ቁ. | ዓረፍተነገር |
|---|---|---|
| ትርንጎ<br>ያግዛል<br>እነሰለሞን<br>ናት<br>እሱባለው | 1 | _________ ዘወትር ያጠናሉ። |
| | 2 | በላይነሽ ጎበዝ ተማሪ _________። |
| | 3 | _________ ወደትምህርትቤት ሄደ። |
| | 4 | _________ ነጭ ልብስ ለበሰች ። |
| | 5 | በቀለ ቤተሰቡን _________። |

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በምን ይዳብራል?
2. ቤተመጻሕፍት ውስጥ ይዞ መግባት የማይፈቀዱ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. የትምህርትቤት ሕጎችን ማክበር የሚገባው ማን ነው?
4. በትምህርትቤት ሕጎችና ደንቦች ባይኖሩ ምን ችግር የሚፈጠር ይመስላችኋል?

## ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተገቢ ቃላትን በመምረጥ በባዶው ቦታ ላይ አስገቡ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ቤተመጻሕፍት | 2. ማክበር | 3. ፀጥታ | 4. ታላላቆችን | 5. ማራኪ |

ምሳሌ፦ ወርቂ ማራኪ የፊት ገጽታ አላት፡፡

1. ____________ ማክበር ጠቃሚ ባህላችን ነው፡፡
2. የሚያነቡ ተማሪዎች እንዳይረበሹ________ ያስፈልጋል፡፡
3. ________ ገብቶ የሚያነብ ተማሪ በትምህርቱ ይጎብዛል፡፡
4. የቤተመጻሕፍት ሕግ ____________ ተገቢ ነው፡፡

## መጻፍ

የቃላትን ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፏቸው፡፡

ምሳሌ፡- ልብስ አረንጓዴ ለበሰች ሞሚና

ሲስተካከል → ሞሚና አረንጓዴ ልብስ ለበሰች፡፡

1. መጣ አህመድ ትናንት፡፡
2. ታጠናለች ጥሩሰው ዘወትር፡፡
3. በጣም ወይኒቱ ተደሰተች፡፡
4. ተንከባከበ ችግኙን ብርሃኑ፡፡
5. ተማሪ ጎበዝ ይነሳል በጠዋት፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## የትምህርትቤት ሕግና ደንብ አከባበር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ሞሚናና ተሰማ በትምህርትቤት ለምን ተወዳጅ ሆኑ?
2. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
3. በምንባቡ ውስጥ ለአጋጠመው ችግር ምን መፍትሔ ተሰጠ?

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ዋናውን ቃል ከቅጥያው ነጥሉ።

ምሳሌ፦ ቤቶች → ቤት -ኦች

1. ቤትህ 2. ወንድምሽ 3. ወንበሮች 4. አልጋዎች

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በጽሁፍ መልሱ።

1. ቤተመጻሕፍት ውስጥ ይዞ መግባት የሚፈቀዱት ምን ምን ናቸው?
2. የቤተመጻሕፍት ሕጎች ምን ምን ናቸው?
3. የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ በሶስት ዐረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ።

### ቃላት

በቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ተጠቅማችሁ ዐረፍተነገሮችን መሥርቱ።

1. ሥርዓት 2. መንከባከብ 3. የደንብ ልብስ 4. ተጠቃሚ

## መጻፍ

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በድርጊት ቅደምተከተል አስተካክላችሁ ጻፉ::

| | |
|---|---|
| 1. መሬቱን አረሰ:: | 1. በሬዎችን በጧት አውጥቶ አበላ:: |
| 2. ወደእርሻው ሄደ:: | 2. ______________________ |
| 3. በሬዎችን በጧት አውጥቶ አበላ:: | 3. ______________________ |
| 4. በሬዎችን ጠመደ:: | 4. ______________________ |
| 5. በሬዎችን ፈትቶ ወደቤቱ ተመለሰ:: | 5. ______________________ |

## ግለንባብ

### አርአያነት በተግባር

የተማሪዎች አርአያነት እንዴት ይገለጻል? ተማሪዎች በትምህርትቤት፣ በቤታቸውና በአካባቢያቸው ሥርዓትን የሚያከብሩ ትጉህና ታታሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ንብረት በመጠበቅና በመንከባከብ፣ ወላጆቻቸውን በትርፍ ጊዜ በመርዳትና በርትቶ በማጥናት ወርቃማ ጊዜያቸውን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡



★★★"ከዚህ በላይ የቀረበው ጽሑፍ ስለተማሪዎች ምን አለ?"★★★


አንዳንድ ተማሪዎች እነዚህን ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ከመምህራን፣ ከትምህርትቤቱ ማህበረሰብና ከወላጆቻቸው ጋር ሲጋጩ ይታያሉ፡፡ የትምህርትቤት ንብረት በማበላሸታቸው ትምህርትቤታቸውንና ወላጆቻቸውን ይጎዳሉ፡፡ የደንብ ልብስ ባለመልበሳቸው ለቅጣት ይዳረጋሉ፡፡ እርስበርስ በመጣላት ይጎዳዳሉ፡፡ ባለማጥናታቸው ጥሩ ውጤት አያስመዘግቡም፡፡ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ተማሪዎችን ይጎዳል፤ ወላጆቻቸውንና መምህሮቻቸውን ያሣዝናል፡፡

በሌላ በኩል ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው የሚጠበቁባቸውን ተግባራት የሚያከናውኑ ወጣቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ለሌሎች ተማሪዎችም ግንዛቤ በመስጠት እንዲለወጡ ያደርጋሉ፡፡ ሀላፊነታቸውን መወጣት በመቻላቸው የወላጆቻቸውን፣ የትምህርትቤታቸውንና የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ በጥሩ ስም ያስጠራሉ፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

ምሥጉኗ መምህርት ተሸለመች



### ቃላት

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን ጻፉ።

1. ታማኝነት
2. ሀቀኝነት
3. ንጽህና
4. ስርዓት ማክበር
5. ሙሰኛ አለመሆን

### ማጣመር

በሚከተሉት ክፍት ቦታዎች ላይ ተስማሚ የሆኑ ስሞችን ወይም ግሶችን ሙሉ።

ምሳሌ፦ ገበየሁ ወደትምህርትቤት ____________ ።

ገበየሁ ወደትምህርትቤት ሄደ።

1. ____________ ትምህርቱን ይወዳል።
2. ____________ ከሶስተኛ ክፍል አንደኛ ሆነች።
3. ሞሚና ቤተመጻሕፍት ገብታ ____________።
4. አገሬ ቤተሰቧን ____________።
5. ____________ የቤት ሥራውን ሠራ።

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. በአርአያነት የሚጠቀሱ ተማሪዎች ምን ምን ተግባራትን የሚያከናውኑ ናቸው?
2. ወጣቶች ተጠቃሚ የሚሆኑት ምን ሲያደርጉ ነው?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ ከሶስት በማይበልጡ ዐረፍተነገሮች ግለጹ።

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዐረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

1. ወርቃማ   2. ማህበረሰብ   3. ንብረት   4. አርአያነት

## መጻፍ

በጥሩ አርአያነቱ የምትከተሉትን ሰው ተግባራት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በአምስት ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ምሥጉኗ መምህር ተሸለመች

በማዳመጥ ምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. የትምህርትቤቱ ርዕሰ መምህር ዘይነባን ምን አሏት?
2. መምህር ዘይነባ ከወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ጋር በመገናኘት ምን አደረገች?
3. የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ለመምህርት ዘይነባ ምን አደረገላት?

## መነጠል

ስሞችን፣ የስም ገላጮችን፣ የግስ ገላጮችንና ግሶችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ | | የስም ገላጭ | ስም | የግስ ገላጭ | ግስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጎበዙ አርሶአደር በፍጥነት መጣ፡፡ | ጎበዙ | አርሶ አደር | በፍጥነት | መጣ |
| 2 | ጠይሟ ሠልጣኝ በሩጫ አሸነፈች፡፡ | | | | |
| 3 | ረጅሙ ዛፍ ዛሬ ተቆረጠ፡፡ | | | | |
| 4 | አጭሯ መምህር ትናንትና ሄደች፡፡ | | | | |

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ተማሪዎች በአብዛኛው በአርአያነት ማንን የሚከተሉ ይመስላችኋል?
2. የምንባቡ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?

## ቃላት

የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ተገቢውን ቃል በመምረጥ አሟሉ፡፡

1. ትህትና  2. ታታሪ  3. ሲጋጩ  4. ግንዛቤ

1. ሙሉነህ ሳይቆጣ ሰዎችን በ ______________ ያስተናግዳል ፡፡
2. ከአስቴር ገለጻ በቂ ______________ አግኝቻለሁ፡፡
3. ወርቅነሽ ______________ ሠራተኛ በመሆኗ ተሸለመች ፡፡
4. ሰዎች ______________ ገላጋይ ያስፈልጋቸዋል፡፡

## መጻፍ

የቃላቱን ቅደምተከተል በማስተካከል ትክክለኛ ዐረፍተነገሮችን ጻፉ፡፡


ምሳሌ፡- ሄደ ታከለ ትናንት፡፡

ታከለ ትናንት ሄደ፡፡

1. ያጠናል ዘወትር ብርሃኑ፡፡
2. በጣም ወይንሸት ተደሰተች፡፡
3. ተንከባከበች ችግኙን ዓለሚቱ፡፡
4. ተማሪ ጎበዟ ትነሳለች በጧት፡፡
5. የትምህርትቤት የደንብ ልብስ  አረንጓዴ ለበሰች ራሄል፡፡
6. ጻፈች ለወንድሟ ዘምዘም ደብዳቤ፡፡

## ግለንባብ

### ያረሰ እንደልቡ ጎረሰ





በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በገላን የገጠር ወረዳ የሚኖሩ ወይዘሮ ሐዋና አቶ ሙስጠፋ የሚባሉ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ምንም የከተማ አርሶ አደር ቢሆኑም ክረምትን ብቻ ጠብቀው የሚያመረቱና ምርታቸውን በጥንታዊ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚጠቀሙ በመሆናቸው ኑሯቸው ሊለወጥ አልቻለም፡፡

አንድ ቀን ኑሯቸውን ለመለወጥ ተመካከሩ የውሃ መሣቢያ ሞተር ቢገዙና ከዚያ ተግተው ሠርተው እንደሚለወጡ ተመካከሩ፡፡

***"ከዚህ በመቀጠል ምንባቡ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?"***


ወይዘሮ ሐዋ በቤታቸው ውስጥ በጉተራ ካጠራቀሟቸው ምርት ለቀለብና ለዘር ያህል አስቀርተን ቀሪውን ሽጠን የውሃ መሣቢያ ሞተር እንግዛ ብለው ሃሣብ አቀረቡ፡፡ባለቤታቸውም በሃሣባቸው ተስማሙ፡፡

በዚህም መሠረት ትርፍ ምርታቸውን ሽጠው የውሃ መሣቢያ ሞተር ገዙ፡፡ በዚህም ተጠቅመው ክረምት ከበጋ ማምረት ጀመሩ፤ትርፋማም ሆኑ ለምርታቸው ማንቀሣቀሻም የሚሆን መለስተኛ የጭነት መኪና ገዙ ቤታቸውንም በቆርቆሮ ቤት ቀየሩት፡፡ በዚህም ስራቸው ለአካባቢው አርሶ አደሮች አርአያ ሆኑ፡፡

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የግብርና ጥቅምና መሣሪያዎች




## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ተናገሩ፡፡

1. ግብርና
2. መሣሪያ
3. ሞፈር
4. ቀንበር
5. ምራን
6. እርፍ
7. ማረሻ

## መነጠል

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት ስም፣ የስም ገላጭ፣ የግስ ገላጭና ግሥ በማለት በምሳሌው መሠረት ለዩ፡፡

| ተ.ቁ | ዓረፍተነገሮች | የስም ገላጭ | ስም | የግስ ገላጭ | ግስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አጭሯ ተወዳዳሪ በፍጥነት ሮጠች፡፡ | አጭሯ | ተወዳዳሪ | በፍጥነት | ሮጠች፡፡ |
| 2 | ወፍራሙ ልጅ ዛሬ ሄደ፡፡ | | | | |
| 3 | ጎበዙ ተማሪ በየቀኑ ያጠናል፡፡ | | | | |
| 4 | አሮጊቷ ሴት በጊዜ ተኙ፡፡ | | | | |
| 5 | ረባሹ ተማሪ በጣም ተመከረ፡፡ | | | | |

## 2ኛ ቀን


## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ::

1. እነወይዘሮ ሐዋ ለምን የመስኖ እርሻ ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆዩ?
2. እነወይዘሮ ሐዋ በጎተራ ያስቀመጡት ምን ነበር?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል ቀይራችሁ ጻፉ?

## ቃላት

የእርሻ መሣሪያዎች ስያሜዎችን ከሥዕሉ ጋር አዛምዱ::

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. እርፍ |  |
| 2. ማረሻ | |
| 3. ቀምበር | |
| 4. ምራን | |
| 5. ሞፈር | |



## መጻፍ

ከእርሻ መሣሪያ ክፍሎች ውስጥ አምስቱን በመምረጥ አገልግሎታቸውን በአንዳንድ ዓረፍተነገር ጻፉ::

## 3ኛ ቀን



### ማዳመጥ

## የግብርና ጥቅምና መሣሪያዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ባህላዊ የእርሻ መሣሪያዎች በአብዛኛው የሚሠሩት ከምንድን ነው?
2. የግብርና ምርቶች ከቤት ውስጥ ፍጆታ በተጨማሪ ለምን ይውላሉ?
3. የአገራችን አርሶአደሮች ከዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች ይልቅ በባህላዊ የእርሻ መሣሪያዎች ለምን ይጠቀማሉ?
4. የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ በቃል ግለጹ፡፡



### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- እጁ → እጅ - ኡ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፀጉሩ | 3. ፊቱ | 5. ጣቱ |
| 2. አንገቱ | 4. እግሩ | |

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ወይዘሮ ሐዋና አቶ ሙስጠፋ ችግሮቻቸውን ለማቃለል ምን አደረጉ?
2. እነወይዘሮ ሐዋ ምርታቸውን ከሸጡ በኋላ ገንዘቡን ምን አደረጉት?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በሶስት ዓረፍተነገሮች አሳጥሩ፡፡

## ቃላት

ተገቢ ቃላትን በመምረጥ የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አሟሉ፡፡

| ቀለብ | ምርቱ | ስልቻ | ከተተ | ጥበቃ | ልማት |
|---|---|---|---|---|---|

ምሳሌ፦ አርሶአደሯ በልማት ንቁ ተሣታፊ ሆነች፡፡

1. አርሶአደሩ ከ ________ የተረፈውን ምርት ሸጠ፡፡
2. በሪሁን ምርቱን በጎተራ ________________፡፡
3. አህመድ ጎተራ ስለሌለው ምርቱን በ _______ ከተተው፡፡
4. ደኖች እንዳይጨፈጨፉ _______ ይደረግላቸዋል፡፡
5. በርትቶ የሠራ አርሶአደር _______ ይጨምራል፡፡

## መጻፍ

"ታታሪ አርሶአደር ብሆን" በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ግለንባብ

# አዝርዕትና ወቅቶቻቸው



ትጉህ አርሶአደሮች ወቅቶችን ለይተው ያውቃሉ፤ በሚገባም ይጠቀሙባቸዋል። በሀገራችን በዓመቱ ውስጥ ያሉ ወቅቶች በአራት ይከፈላሉ። እነሱም መኸር(መፀው)፣ በጋ (ሃጋይ)፣ ፀደይ (በልግ) እና ክረምት በሚባል ይታወቃሉ። መኸር (መፀው) ከመስከረም እስከ ህዳር፣ በጋ (ሃጋይ) ከታህሳስ እስከ የካቲት፣ ፀደይ (በልግ) ከመጋቢት እስከ ግንቦት፤ ክረምት ከሰኔ እስከ ነሐሴ ያሉትን ወራት ያካትታሉ።

★★★"ከዚህ በላይ የተነበበውን በማስታወስ በዓመት ውስጥ ያሉትን ወቅቶች ዘርዝሩ።"★★★


ስለሆነም አርሶአደሮች በአካባቢያቸው ከሚገኙ የግብርና ልማት ባለሙያዎች ጋር በመመካከር በበልግ ወቅት ተገቢውን የማሳ ዝግጅት ያደርጋሉ። በወቅቱ መጨረሻም የምርት ማሣደጊያ ግብአቶችን ማለትም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በመጠቀም ዘር ይዘራሉ። ከሚዘሯቸው የአዝርዕት ዓይነቶች ውስጥ ለምሳሌ የቅባት እህሎች ሰሊጥ፣ ኑግ፣ ሱፍና ጎመንዘር የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። በክረምት ወቅት ቡቃያው ይታረማል፤ ከፀረ ሰብል አውሬዎች ይጠበቃል። በዚህ ዓይነት እንክብካቤ አዝርዕቱ አድገውና አብበው ሲያፈሩ በመኸር ወቅት ይታጨዳሉ። ነዶው እየተሰበሰበ ይከመራል። በመጨረሻም አውድማ ተዘጋጅቶ ከተወቃ በኋላ ምርቱ ወደጎተራ ይገባል።

በበጋ ወቅት የተመረተው ምርት ለምግብ ፍጆታና ለዘር የሚበቃው ተለይቶ ይቀመጣል። ተራፊው ምርት ገበያ ወጥቶ ይሸጥና ለተለያዩ ጥቅም ሰጭ ተግባራት ይውላል።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## በባለሙያ ምክር የተለወጠው ወጣት



### ቃላት

1. የሚከተሉትን የጓሮ አትክልቶች በየምድባቸው ፃፉ፡፡

| የጓሮ አትክልት | በጥሬ የሚበሉ | በስለው የሚበሉ |
|---|---|---|
| ሸንኩርት | | - |
| ቲማቲም | - | |
| ቃሪያ | | |
| ቆስጣ | | |
| ሰላጣ | ሰላጣ | |
| ጎመን | | ጎመን |
| ካሮት | | |
| ዱባ | | |
| ዝኩኒ | | |

2. በሰንጠረዡ ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት የስም ወይም የግስ ገላጭ መሆናቸውን በመለየት፣ በምሳሌው መሠረት "✓" ምልክት አስቀምጡ።

| ተ.ቁ | ዐረፍተነገር | የስም ገላጭ | የግሥ ገላጭ |
|---|---|---|---|
| 1 | መልከኛዋ ሴት በቁንጅና ውድድር አሸነፈች። | ✓ | |
| 2 | ወፍራሙ ወታደር ዛሬ መጣ። | | ✓ |
| 3 | ዘመነ ቀይ ሱሪ ለብሷል። | | |
| 4 | ረጅሟ ልጅ ዛሬ ሄደች። | | |
| 5 | አስተዋይ ተማሪ ሁልጊዜ ይሠራል። | | |
| 6 | ኀበዟ ዋናተኛ ትናንት ተሸለመች። | | |

## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. ለምግብ ፍጆታና ለዘር የሚፈለገው ምርት ከተቀመጠ በኋላ ሌላው ምን ይደረጋል?
2. አዝርዕት ወቅታቸውን ጠብቀው ባይዘሩ ምን ችግር ይፈጠራል?
3. ወቅቶች በሁሉም የአገራችን ክፍሎች በተመሳሳይ ጊዜ የሚከሰቱ ይመስላችኋል?
4. የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ በሁለት ዐረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ፃፉ።

## ቃላት

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በምሣሌው መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ::

ምሳሌ፦ ማሳው ለእርሻ ተዘጋጀ::

ማሳ → የእርሻ ቦታ

1. ምርጥ ዘር የተጠቀሙ አርሶአደሮች ውጤታማ ሆኑ::
2. የተለያዩ አዝርዕት መመገብ ሰውነት ይገነባል::
3. ፀረተባይ መድኃኒት በመርጨት ተባዮችን ተከላከሉ::
4. አርሶአደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ::

## መጻፍ

የስምና የግሥ ገላጭ ያላቸውና ሥርዓተነጥባቸው የተሟላ አምስት ዐረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት ፃፉ::

ምሳሌ፦ አለሚቱ ሰፊ ቀሚስ በጣም ትወዳለች::

ሰፊ → የስም ገላጭ

በጣም → የግሥ ገላጭ

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### በባለሙያ ምክር የተለወጠው ወጣት

በማዳመጥ ምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ::

1. በወጣት ጋዲሳ አካባቢ ከሚመረቱ ምርቶች አምስቱን ዘርዝሩ::
2. የወጣት ጋዲሳ ምርት እንደጎረቤቱ ማደግ ያልቻለው ለምንድን ነው?
3. ለወጣቶች የሙያ ምክር ማን ሰጣቸው?

## መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ዋናውን ቃልና ቅጥያውን ነጣጥላችሁ ፃፉ::

ምሳሌ፦ ቤቴ → ቤት - ኤ

ቤታችን → ቤት - ኣችን

1. ልብሴ
2. እናታችን
3. ወንድሜ
4. ደብተሬ
5. መምህራችን

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በጽሁፍ መልሱ::

1. የቅባት እህሎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. ለአርሶአደሮች ሥራ የማይበዛበት ወቅት የትኛው ነው?
3. አርሶአደሮች ወቅቶችን ጠብቀው እንዲያመርቱ የሚያደርጓቸው ምንድን ናቸው?
4. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀፅ ሀሳብ ባጭሩ ግለጹ::

## ቃላት

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ::

1. በክረምት አካባቢው በሙሉ ለምለም ነው::
2. በበጋ ወቅት የአብዛኛዎቹ ተክሎች ቅጠል ይረግፋል::
3. አርሶአደሮች በፀደይ ወቅት ተግተው ይሠራሉ::
4. እንስሳት በበልግ ወራት መቦረቅ ይጀምራሉ::

## መጻፍ

የምታውቋቸውን አዝርዕት ጥቅሞች በአምስት ዐረፍተነገሮች ግለጹ:: በዐረፍተነገሮች ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ::

## ግለንባብ

### እንክብካቤና ጥበቃ ለደኖች



በአካባቢያችን ደኖች በመመናመናቸው የምንጮችና የወንዞች መጠን ቀነሰ፤ የአየር ንብረት መቀያየር ጀመረ። የአካባቢው የደን ልማት ባለሙያዋ ነዋሪዎችን ሰብስባ “የአካባቢው ደኖች እየተመናመኑ ናቸው፤ ምንጮችና ወንዞችም መጠናቸው እየቀነሰ እና አየር ንብረቱም እየተዛነፈ ነው። ስለዚህ ችግሩን ለመከላከል በጋራ ምን ብናደርግ ይሻላል?” በማለት ሀሳብ አቀረበች። ከነዋሪዎቹም መካከል አንዱ ተነስቶ “አሁን የቀረበውን ሃሳብ ሁላችንም የምንጋራው ስለሆነ አካባቢን የማልማትና የመጠበቅ ሥራ መጀመር አለበት” አለ። ቀጠሉና ሌላው ነዋሪ “እኔም ይሄ ጉዳይ ሲያሳስበኝ ነበር። የደን ልማት ባለሙያዋ የሥራ ዕቅድ ያዘጋጁልንና የአካባቢ ልማትና ጥበቃ ሥራው ይጀመር” አሉ። ሁሉም በሀሳቡ ተስማሙ።

✶✶✶“ነዋሪዎችና የደን ልማት ባለሙያዋ ምን የሚሰሩ ይመስላችኋል?”✶✶✶

የደን ልማት ባለሙያዋ የድርጊት መርሃግብር አዘጋጀች። በቅድሚያ በተራሮቹ ላይ የዕርከን ሥራ ተሠራ። ቀጥሎ ለችግኞች መትከያ ጉድጓዶች ተዘጋጁ። ክረምቱ ሲገባ ችግኞች ተተከሉ። የተተከሉት ችግኞች ከእንስሳትና ከሰው ንክኪ ተጠብቀው አደጉ። የተራቆቱት ተራሮች ቀስበቀስ ደን ለበሱ። በደኑ ውስጥ የዱር እንስሳትና ወፎች መራባት ጀመሩ። ወንዞችና ምንጮች መጠናቸው ጨመረ። የአካባቢው ህብረተሰብ የመስኖ ልማት ተጠቃሚ መሆን ቻለ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነዋሪዎቹ በጥረታቸው ያለሚቸውን ዛፎች እንደልጆቻቸው ይንከባከቧቸውና ይጠብቋቸው ጀመር።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



## የደን ጭፍጨፋና ውጤቱ

### ቃላት

በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ" ረድፍ ከተዘረዘሩት ፍቻቸውን በመፈለግ አዘምዱ።

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1. | ማልማት | ሀ. | መቀነስ (ማነስ) |
| 2. | ደን | ለ. | የዝናብ አለመኖር |
| 3. | ድርቅ | ሐ. | ዝርያቸው ከሌላ ቦታ የማይገኝ |
| 4. | ብርቅዬ | መ. | ጫካ |
| 5. | እጥረት | ሠ. | ማሳደግ፣ ማስፋፋት |

### ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላት በምሣሌው መሠረት ቅጥያዎቹን ከቃላቱ ጋር በማጣመር ባለቅጥያ ቃላት መሥርቱ።

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | ቅጥያ | ቃል |
|---|---|---|---|
| 1 | ሹራብ | -ኤ<br>-ኣችን | ሹራቤ |
| 2 | እግር | | እግራችን |
| 3 | ኮት | | |
| 4 | ቀሚስ | | |
| 5 | እናት | | |
| 6 | ወንበር | | |

## 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ::

1. ደኖች በመጨፍጨፋቸው ምን ተከሰተ?
2. በሁሉም ተቀባይነት ያገኘው ሃሳብ ምን ነበር?
3. ለወፎችና ለዱር እንስሳት የተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምን ነበር?
4. የምንባቡን ዋና መልዕክት በሶስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ::

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት መርጣችሁ በምሳሌው መሠረት በክፍቱ ቦታ ላይ ሙሉ::

| የደን | ጭፍጨፋ | መራቆትን | ድርቅ | ይሰደዳሉ | ይሸረሸራል |
|---|---|---|---|---|---|

ምሳሌ፦ <u>የደን</u> መጨፍጨፍ ድርቅን ያመጣል::

1. የደኖች መጨፍጨፍ የመሬት ___________ ያስከትላል::
2. ደኖች ሲጨፈጨፉ ዝናብ ጠፍቶ ___________ ይሆናል::
3. ደኖች ሲጨፈጨፉ አፈሩ በጐርፍ ___________::
4. ድርቅና ረሀብ ሲኖር ሰዎች ___________::
5. የደኖችን ___________ እንከላከል::

## መጻፍ

ለደኖች መጨፍጨፍ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ አጫጭር ዐረፍተነገሮች ግለጹ:: የጻፋችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የደን ጭፍጨፋና ውጤቱ**

**የማዳመጥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።**

1. ደኖች የተመናመኑበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ብርቅዬ የዱር እንስሳትና ዓዕዋፍ ለምን ተሰደዱ?
3. የምንባቡ ዋና ሃሳብ (መልእክት) ምንድን ነው?

### ማጣመር

**"-ኤ" ወይም "-ኣችን" የሚሉት ቅጥያዎች ያሉባቸው አሥር ቃላት ጻፉ።**

ምሳሌ፦ እህት - ኤ → እህቴ

እህት - ኣችን → እህታችን

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።**

1. "እኔንም ይህ ጉዳይ ያሳስበኝ ነበር" ያሉት ማን ናቸው?
2. የደን ባለሙያዋ ለነዋሪዎች ምን ሀሳብ አቀረበች?
3. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
4. የምንባቡን የመጀመሪያ አንቀጽ ሀሳብ በሁለት ዓረፍተነገሮች ግለጹ።

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር ያሉትን ቃላትና ሀረጎች በ“ለ” ሥር ካሉት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ::

| | “ሀ” | | “ለ” |
|---|---|---|---|
| 1. | ዛፎችን መንከባከብ | ሀ. | ዕፅዋትን ማውደም |
| 2. | የቤት እንስሳት | ለ. | ተክሎችን መጠበቅ |
| 3. | የዱር እንስሳት | ሐ. | ለማዳ ያልሆኑ እንስሳት |
| 4. | የደን ጭፍጨፋ | መ. | ለማዳ እንስሳት |

## መጻፍ

ችግኞችን ከመትከል ጀምሮ ተንከባክቦ እስከማሳደግ ያለውን የተግባር ቅደምተከተል በምሳሌው መሠረት በአምስት ዐረፍተነገሮች ግለጹ:: በጽሁፉ ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ::


ምሳሌ:- ለችግኝ መትከያ ጉድጓድ ይቆፈራል::

22ኛ ሳምንት



## ግለንባብ

### ዕደጥበባትና ውጤታቸው




በሀገራችን በገጠርም ሆነ በከተማ ባህላዊ የዕደጥበብ ሙያዎች አሉን፡፡ እነዚህም የሽመና፣ የብረታብረት፣ የእንጨት፣ የቆዳና የሸክላ ሥራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ የዕደጥበብ ሙያዎች የዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ሙያዊ ሥልጣኔ) መሠረት ናቸው፡፡ ለባለሙያዎቹ የገቢ ምንጭ ይፈጥራሉ፡፡ የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ፍላጎቶችም ያሟላሉ፡፡ አርሶአደሩ የሚያርስበት ማረሻና የሚያጭድበት ማጭድ ባብዛኛው በባህላዊ የብረታብረት ሠራተኞች ይመረታሉ፡፡

ከሀገራችን አልፎ ወደውጭ በመላክ አድናቆትን ያተረፉት የሽመና ልብሶቻችንና ልዩ ልዩ ጥበቦቻችን የባህላዊ ሽመና ሥራ ውጤቶች ናቸው፡፡ በከተማችን ጉለሌ ክ/ከተማ ውስጥ ቀጨኔ መድሐኒዓለም የሚባል አካባቢ አለ፡፡፡ በአካባቢው በተደራጁ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚመረቱ ልዩ ልዩ የሸክላ ሥራ ውጤቶች በጥራታቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው እጅግ በጣም ይፈለጋሉ፡፡ በሽሮ ሜዳ እየተሠሩ ያሉ የሽመና ውጤቶች ውበታቸው የሀገር ውስጡንም ሆነ የውጭውን መህበረሰብ ዐይን ይማርካሉ፡፡ እነዚህ ዕደ-ጥበቦች የሙያውን ታላቅነት አመላካች ናቸው፡፡

መንግሥትና ህብረተሰቡ ለእነዚህ ባህላዊ የዕደጥበባት የሥራ ውጤቶች ከፍተኛ ትኩረት እየሰጧቸው በመሆኑ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙትን የሙያውን ባለቤቶች በማህበረሰብ ሥልጠና ማዕከላት በማደራጀት ሙያው እየበለፀገ ነው፡፡ እነዚህን የባህላዊ ዕደጥበባት የሥራ ዓይነቶች ከዚህ በበለጠ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**በመደራጀታቸው የተለወጡ ወጣቶች**

### ቃላት

በቡድን በመወያየት ለሚከተሉት ቃላት ፍቺቸውን ጻፉ::

1. ሥራ 2. ግብርና 3. ንግድ 4. ግምበኝነት 5. አናጢነት

ምሳሌ:- ግብርና → የእርሻ፣ የእንስሳትና ልማትና የአትክልት ልማት ሙያ

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ላይ ያሉትን ቅጥያዎች በመነጠል በባዶ ቦታዎች ላይ ሙሉ::

| ተ.ቁ. | ቃል | ዋና ቃል | ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ቤቴ | ቤት | -ኤ |
| 2 | ልብሳችን | | |
| 3 | ደብተርህ | | |
| 4 | ክፍልሽ | | |
| 5 | መምህራችሁ | | |
| 6 | አገሬ | | |

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ::

1. የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሠረት የሚባሉት ምንድን ናቸው?
2. በዕደጥበብ የሚመረቱ ምርቶች ምን ምን ናቸው?
3. በገጠርም ሆነ በከተማ የምናገኛቸውን የዕደጥበብ ሙያዎች ዘርዝሩ?
4. መንግሥትና ህብረተሰቡ ለዕደጥበብ ሙያተኞች ምን ዕገዛ ሊያደርጉላቸው የሚገባ ይመስላችኋል?

## ቃላት

በቡድን ተደራጁ፤ አንዱ ቡድን ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱን ቃል ወይም ሐረግ ሲጠራ ሌላው ቡድን በቃሉ ወይም በሐረጉ ዐረፍተነገር ይሠራል:: ዐርፍተነገር የሠራው ቡድን በተራው ቃል ወይም ሐረግ ሲጠራ ሌላው ቡድን ዐረፍተነገር ይሠራል:: በዚህ ዓይነት ቃላቱና ሐረጋቱ አስኪያልቁ ጨዋታው ይቀጥላል::

ምሳሌ፦ <u>ቡድን "ሀ"</u> — <u>ቡድን "ለ"</u>

ሸመና → አስቴር በሸመና ሙያ ተሰማርታለች::

ከበደ በዕደጥበብ ሙያ ሰለጠነ ← ዕደጥበብ

1. እንጨት ሥራ
2. ቆዳ ሥራ
3. መካኒክነት
4. ሾፌርነት
5. ሸክላ ሥራ
6. ሕክምና
7. መድኃኒት ቅመማ

## መጻፍ

"ልሠማራበት የምፈልገው የዕደጥበብ ሙያ" በሚል ርዕስ አምስት አጫጭር ዐረፍተነገሮች ጻፉ:: በዐረፍተነገሮች ውስጥም ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### በመደራጀታቸው የተለወጡ ወጣቶች

በማዳመጥ ምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ::

1. የናትናኤል ጓደኛ የተሠማራበት ሙያ ምንድን ነው?
2. ባሕላዊ የዕደጥበብ ሙያዎች ለወደፊቱ ምን መሆን ይገባቸዋል?
3. የምንባቡን መልዕክት ባጭሩ ግለፁ::

## ማጣመር

የሚከተሉትን ዋና ቃላትና ቅጥያዎችን በማጣመር ባለቅጥያ ቃላት መሥርቱ፡፡

1. እርሳስ - ኤ
2. ወንበር- ኣችን
3. እግር -ኤ
4. እናት -ኣችን
5. ወረቀት - ኤ

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ማጭድና ማረሻ በአብዛኛው የሚመረቱት በማን ነው?
2. የዕደጥበብ ውጤቶችን በዘመናዊ መንገድ ማምረት ጥቅሙ ምንድን ነው?
3. ወደውጭ በመላክ አድናቆትን ያተረፉት የዕደጥበብ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?
4. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሶስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ?

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ” ሥር ከሚገኙት ፍቺቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሸመና | ሀ. ከሸክላ አፈር ልዩ ልዩ ዕቃዎችን መሥራት |
| 2. ዕደጥበብ | ለ. ከአንስሳት ቆዳ ልብሶችንና ልዩ ልዩ ዕቃዎችን መሥራት |
| 3. ብረታብረት ሥራ | |
| 4. የሸክላ ሥራ | ሐ. ልዩ ልዩ የእጅ ሙያ |
| 5. የቆዳ ሥራ | መ. ከጥጥ ልዩ ልዩ ልብሶችን መሥራት |
| | ሠ. ከብረት ልዩ ልዩ ዕቃዎችን መሥራት |

## መጻፍ

በቤታችሁ ውስጥ የሚገኙ የዕደጥበብ ሙያ ውጤቶችን ጥቅም ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 23ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### የእነሕይወት ተሞክሮ



በአንድ አነስተኛ ከተማ ውስጥ በር፣ መስኮትና የመሳሰሉትን የሚሠራ የብረታብረት ሠራተኛ አልነበረም:: በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ ይቸገር ነበር::

በብረታብረት ሙያ የሠለጠኑ ሦስት የአካባቢው ወጣቶች በሙያቸው ሥራ ለመጀመር አሰቡ:: ህይወት ሥራውን ለመሥራት ካሰቡት ወጣቶች አንዷ ስትሆን "በአካባቢው ሥራውን ለመጀመር ምን ማድረግ እንደሚጠበቅብን ብንነጋገር?" አለች::

በዕውቀቱ የሚባለው ሌላው ወጣት "መጀመሪያ እንደራጅ፤ ከዚያ ስለሥራው አዋጭነት ጥናት እናድርግ" አለ:: ሦስተኛው ወጣት አለሙ ደግሞ "ከመደራጀታችን በፊት ጥናት ብናካሂድስ?" አለ:: ህይወት "በቅድሚያ መደራጀቱ ጥሩ ነው:: የሥራ ቦታና የመሥሪያ ገንዘብ በብድር ማግኘት እንችላለን" አለች::

✶✶✶" እነሕይወት የሥራ ቦታና የመሥሪያ ገንዘብ እንዴት የሚያገኙ ይመስላችኋል?"✶✶✶

ወጣቶቹ ተደራጅተው ጥናት ለማድረግ ተስማሙ፤ ተደራጁ፤ ጥናት በማካሄድ የሥራውን አዋጭነት አረጋገጡ:: ጥሩ የመሥሪያ ቦታ አገኙ:: ገንዘብ በብድር ተሰጣቸው:: የሚሠሩትን ሥራ ለይተው አወቁ:: ሥራዎችን ተከፋፈሉ:: የሥራ ቦታና ባለሙያን በመለየት የሥራ ድልድል አደረጉ:: ሥራው ተጀመረ:: የአካባቢው ህብረተሰብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆኑ ችግሩ ተቃለለ::

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የሥራ ዕቅድ

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺዎች ተናገሩ።

1. ዕቅድ    2. ወቅት    3. ዓላማ    4. መከፋፈል

## ማጣመር

በሚከተሉት የተሰመረባቸው ቃላት ላይ ተስማሚ ቅጥያ በመጨመር ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፉ።

| ተ.ቁ | ያልተስተካከሉ ዐረፍተነገሮች | የተስተካከሉ ዐረፍተነገሮች |
|---|---|---|
| 1 | ወደቤት ሂጅ። | ወደቤትሽ ሂጂ። |
| 2 | በመኪና ሣይሆን በእግር ነይ። | |
| 3 | በጠዋት ወደቤት ሄዱ። | |
| 4 | ልብሱን በእጅ አጠበ። | |
| 5 | ሁልጊዜ በእግር ተጓዙ። | |

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. ሶስቱ ወጣቶች የሰለጠኑበት ሙያ ምን ነበር?
2. ወጣቶቹ በምን ተስማሙ?
3. የምንባቡን ዋና ሃሳብ ባጭሩ ግለጹ።

## ቃላት

በሳጥን ውስጥ ከቀረቡት ቃላት መካከል ተገቢውን ቃል በመምረጥ ክፍት ቦታውን አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| እንደራጅ | አዋጭነቱን | ጥናት | ድልድል |

1. ወጣቶች በማህበር __________ በሚለው ሃሳብ ተስማሙ።
2. ሠራተኞች የሥራ __________ አደረጉ።
3. ወጣቶች ወደሥራ ከመሠማራታቸው በፊት በጥናት __________ አረጋገጡ።
4. በ __________ ላይ ተመስርቶ የሚሠራ ሥራ ያዋጣል።

## መጻፍ

በየቀኑ የምታከናውኗቸውን ተግባራት ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ተገቢውን ሥርዓተነጥቦችን ተጠቅማችሁ ፃፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የሥራ ዕቅድ

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. ዕቅድ ስናቅድ ልንከተላቸው የሚገቡ ቅደምተከተሎች ምን ምን ናቸው?
2. በድርጊት መርሃግብር ሊካተቱ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. የዕቅድ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

## መነጠል

የስም ገላጮችን፣ ስሞችን፣ የግሥ ገላጮችንና ግሶችን በምሳሌው መሠረት ለይታችሁ አውጡ።

| ተ.ቁ | ዓርፍተ ነገር | የስም ገላጭ | ስም | የግሥ ገላጭ | ግሥ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ረጅሙ ልጅ በሩጫ መጣ። | ረጅሙ | ልጅ | በሩጫ | መጣ |
| 2 | ጠይሟ ሠራተኛ ትናንት ሄደች። | | | | |
| 3 | ረባሽ ተማሪ በጣም እጠላለሁ። | | | | |
| 4 | መልከኛዋ ልጃገረድ በጠዋት ተነሳች። | | | | |
| 5 | ፈጣኗ ልጅ በሩጫ አሸነፈች። | | | | |

## 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በፅሁፍ መልሱ።

1. ሶስቱ ወጣቶች ምን ለመሥራት ተስማሙ?
2. ወጣቶች በጥናት ያረጋገጡት ምንድን ነው?
3. እነህይወትን በሰለጠኑበት የኅብረት ሥራ እንዲሠማሩ ያነሳሳቸው ምንድን ነው?
4. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል እንደገና ጻፉት።

## ቃላት

የሚከተሉትን የተሰመረባቸው ቃላትናሐረጋት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሳሌ፡- የተማሪ ዐቢይ ተግባር ትምህርትን መከታተል ነው።

ዐቢይ → ዋና

1. የጨዋታን ጥቅምና ጉዳት በማነጻጸር ተናገሩ።
2. የድርጊት መርሃግብር በማውጣት ወደሥራ ተሰማራች።
3. ዓለሙ የሥራ ክንውን ዘገባ ጻፈ።
4. ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት መለየት ይገባል።

## መጻፍ


በቡድን በመወያየት በትርፍ ጊዜያችሁ ለምትሠሯቸው ሥራዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ በቀረበው ናሙና መሠረት መርሃግብር አውጡ:: ያወጣችሁትን መርሃግብር ለመምህራችሁ አሳዩ::


| ተ.ቁ | የክንውን ጊዜ | የሚከናወኑ ተግባራት | ክንውን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
| 1 | 9:00 - 11:00 ሰዓት | ጨዋታ | ✓ | |
| 2 | 11:00 - 12:00 | ቤተሰብን በሥራ ማገዝ | | ✓ |
| 3 | 12:00 - 2:00 | ማጥናት | ✓ | |
| 4 | 2:00 - 2:30 | ዜና መከታተል | ✓ | |
| 5 | 2:30 - 3:00 | ራት መብላት | ✓ | |

## ግለንባብ

### ሥራና ጥቅሙ

ሥራ የዕድገት መሠረት ነው:: ሥራ በሌለበት ስለዕድገት አይታሰብም:: ሥራ ለሰው ልጅ ህልውና በጣም ጠቃሚ ነው::






ለዚህ ነው “ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው” የሚባለው:: ሥራ ልማትን ፣ ልማት ደግሞ ብልፅግናን ያመጣል:: ልማት ሲኖር የዕውቀት መገኛ የሆኑ ትምህርትቤቶች በየደረጃው ይስፋፋሉ፤ የሰዎች ጤንነት ይጠበቃል፤ ጤናማና ጠንካራ ዜጎች ይፈጠራሉ፤ መንገዶች ይሠራሉ፤ የሰዎች ግንኙነትና የንግድ ሥራዎች ይጠናከራሉ::

ሥራ ባጠቃላይ ዘርፈብዙ ጥቅሞች አሉት:: አርሶአደሩ ጠንክሮ ሲሰራ ምርት ያድጋል፤ ገቢ ይጨምራል፤ ፋብሪካዎቻችን በቂ ጥሬዕቃ ያገኛሉ:: የማምረቻ መሣሪያዎች ይሻሻላሉ:: ሰዎች ለሥራ ያላቸው ፍቅር ይጨምራል:: አመለካከታቸው ይሰፋል:: መተሳሰብና መረዳዳት ይኖራል:: የተማሩና ሥራ ፈጣሪ ዜጎች ይበዛሉ:: ሥራአጥነት አይኖርም:: ሰዎች ለማይጠቅም ወሬ ጊዜ አይኖራቸውም:: ስለሆነም ሁላችንም የሥራን ጥቅም በመገንዘብ ተግተን መሥራትና ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅብናል::

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### አረጋውያን ወደሥራ ተሰማሩ




## ቃላት

በቡድን በመወያየት በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ምሳሌ፡- ወላጆች በአነስተኛ ገቢ ይተዳደራሉ።

1. ዕድገት  2. ልማት  3. መጠለያ  4. ልብስ  5. መንገድ  6. ጤና

## ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ስሞችንና ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን አሟሉ።

ምሳሌ፡- ______________ ትናንትና ተመለሰች።

ዘምዘም ትናንትና ተመለሰች።

1. ጎበዙ ተማሪ ዘወትር ______________።
2. ______________ በደስታ ፈነጠዘች።
3. ሥራ ሕይወት ______________።
4. ታታሪዋ ______________ በፈተና አንደኛ ወጣች።
5. ተማሪዎች የደንብ ልብስ ______________።

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. ለሰው ልጅ ህልውና ጠቃሚ የሆነው ነገር ምንድን ነው?
2. ከሁላችንም የሚጠበቀው ነገር ምንድን ነው?
3. ሰዎች ጊዜያቸውን በማይጠቅም ወሬ እንዳያሳልፉ ምን ማድረግ አለባቸው?
4. የምንባቡን ማጠቃለያ ዋና ሃሳብ የያዘው ዐረፍተነገር የትኛው ነው?

### ቃላት

በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|
| 1. | ማምረቻ | ሀ. አለመጥፋት |
| 2. | ሕልውና | ለ. አተያይ |
| 3. | ፋብሪካ | ሐ. በርትተን |
| 4. | ተግተን | መ. ዘመናዊ ማምረቻ |
| 5. | አመለካከት | ሠ. ምርት ማከናወኛ መሣሪያ |

### መጻፍ

የራሳችሁን ንጽህና ለመጠበቅ ማከናወን የሚገባችሁን ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ግለጹ። በዐረፍተነገሮቹ ውስጥም ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ።

## 3ኛ ቀን



### ማዳመጥ

#### አረጋውያን ወደሥራ ተሰማሩ

በማዳመጥ ምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ወይዘሮ ጌጤነሽ ምን ማድረግ ይወዳሉ?
2. ለመሰብሰብ ፈቃደኛ የሆኑትን አረጋውያን ስብጥር ግለጹ፡፡
3. አረጋውያኑ በምን በምን የሥራ መስክ ተሠማሩ?
4. የምንባቡን ዋና መልዕክት ባጭሩ ግለጹ፡፡



### ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ቅጥያዎችን በማጣመር ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ. | ዋና ቃል | ቅጥያ | ባለ ቅጥያ ቃል |
|---|---|---|---|
| 1 | ፀጉር | -ኤ | ፀጉሬ |
| 2 | አገር | -ኣችን | |
| 3 | እህት | -ህ | |
| 4 | ቤት | -ኣችሁ | |
| 5 | ልጅ | -ኡ | |
| 6 | አባት | -ኣቸው | |

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ሥራ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ሶስቱን ጥቀሱ?
2. “ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው” ማለት ምን ማለት ነው?
3. “ሥራ የዕድገት መሠረት ነው” ስንል ምን ማለታችን ነው?
4. ሰዎች ሥራ እንዲሠሩ የሚያስገድዳቸው ነገር ምንድን ነው?

## ቃላት

በ"ሀ" ሥር ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ"ሥር ከሚገኙት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1. | ጥቅም | ሀ. | ወጪ |
| 2. | ገቢ | ለ. | ውድቀት |
| 3. | ዕድገት | ሐ. | ጥፋት |
| 4. | ልማት | መ. | በሽተኛ |
| 5. | ጤነኛ | ሠ. | ጉዳት |

## መጻፍ

"ለአረጋውያን ምን ማድረግ አለብን?" በሚል መነሻ ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።


## 25ኛ ሳምንት

### ግለንባብ

## የብርቱካንና የዳንኤል መለወጥ

አንዳንድ ወጣቶች የሚኖሩበትን አካባቢ ባህል ባለመከተላቸው ዘመዶቻቸው፣ የዕድሜ አቻዎቻቸው፣ በአጠቃላይም ማህበረሰቡ ያገላቸዋል:: ከእነዚህ ወጣቶች መካከል ብርቱካንና ዳንኤል ተጠቃሽ ናቸው:: እነብርቱካን አንድ ቀን "ወጣቶች የእናቶችና የአባቶች ባህል ባለአደራ ናቸው" በሚል ርዕስ በአንድ ታዋቂ ጋዜጣ ላይ "ባህሎች አኗኗርን፣ አመጋገብን፣ ግጭት አፈታትን፣ የጋብቻና የቀብር ስነስርዓትን የሚያካትት ሰፊ ማህበራዊ እሴቶች በመሆናቸው እነዚህን ባህሎች የማይከተሉ የማህበረሰቡ አባላትን ማህበረሰቡ ያገላቸዋል:: በመሆኑም ብቸኝነት ያጠቃቸዋል፤ በኑሯቸውም ደስተኛ አይሆኑም" የሚለውን ሲያነቡ ቆም ብለው ራሳቸውን ፈተሹ::





***" ወጣቶች ቆም ብለው ስለራሣቸው እንዲያስቡ ያደረጋቸው ምን ይመስላችኋል?"***

አቶ ይልማ ታዋቂ የአካባቢው ሽማግሌ ናቸው:: ብርቱካንና ዳንኤል ችግር እንዳለባቸው ቢያውቁም እንደሌሎቹ የአካባቢው ኗሪዎች፣ ዘመዶቻቸውና የዕድሜ አቻዎቻቸው አላገለሏቸውም:: ከጋዜጣ ላይ ያነበቡትን ነገር የአካባቢውን ባህል ባለመከተላቸው ያጋጠማቸውን እንዲያስቡ አድርጓቸዋል:: በተጨማሪም ከአቶ ይልማ ጋር ከጋዜጣ ላይ ባነበቡት ሀሳብ ዙሪያ መነጋገር ጀመሩ:: "አቶ ይልማ ባህልን ማወቅና መከተል ለምን ይጠቅማል?" አሏቸው:: አቶ ይልማም "ልጆች ባህል ከሰዎች ጋር ተግባብቶና ተጣጥሞ ለመኖር ያስችላል:: አብሮ በመኖር ፣ አብሮ በመስራት ከወላጆች የምንማራቸው ነገሮች ለእኛ ይበጁናል::ልጆች እነዚህን ነገሮች ባለማወቅ፣ ባለማክበርና ባለመከተል የሚጎዱበት ሁኔታ ስላለ ልብ ልትሉ ይገባል" አሏቸው::

እነብርቱካንም ከአቶ ይልማ የተነገራቸውንና ከጋዜጣ ያነበቧቸውን ሀሳብ መተግበር ጀመሩ:: ለአካባቢው ባህል ትኩረት ሰጥተው ባህሉን በመከተላቸው በማህበራዊ ኑሯቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት ደስተኛ ኗሪ ሆኑ::

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

ባህላችን



## ቃላት

1. በቡድን በመወያየት ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን ፃፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ባሕል | 3. ልደት | 5. ቤት አሠራር | 7. ግጭት አፈታት |
| 2. ጋብቻ | 4. አለባበስ | 6. አመጋገብ | 8. ግንኙነት |

2. የስም ገላጮችን፣ ስሞችን፣ የግሥ ገላጮችንና ግሶችን በመለየት በዓይነት በዓይነታቸው መድቡ።

| ስሞች፣ ገላጮችና ግሶች | የስም ገላጭ | ስም | የግሥ ገላጭ | ግሥ |
|---|---|---|---|---|
| መጣ፣ ትናንት፣ ሄደች በፍጥነት፣ ትዕግሥት፣ መጣች፣ ታታሪው፣ ዓለሙ፣ አበባ፣ ፀጉራሟ | ጠይሟ | ትዕግሥት | ትናንት | መጣች |

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. አንዳንድ ወጣቶች ከማህበረሰቡ የሚገለሉት በምን ምክንያት ነው?
2. እነብርቱካን ከጋዜጣው ላይ ያነበቡት ጽሑፍ ርዕስ ምን ይላል?
3. የምንባቡ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
4. ብርቱካንና ዳንኤል የማህበረሰቡን ባህል እንዳይከተሉ ያደረጓቸው ነገሮች ምን ምን ይመስሏችኋል?

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር የሚገኙትን ቃላት በ“ለ” ሥር ከሚገኙት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| | “ሀ” | | “ለ” |
|---|---|---|---|
| 1. | ግንኙነት | ሀ. | ይጠቅሙናል |
| 2. | አመጋገብ | ለ. | ተስማምቶ |
| 3. | ተጣጥሞ | ሐ. | መስተጋብር |
| 4. | ይበጁናል | መ. | አበላል |

## መጻፍ

በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ የምትመለከቷቸውን ነገሮች በአምስት ዐረፍተነገሮች ግለጹ። በዐረፍተነገሮቹ ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ባህላችን

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የባሕል ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የባህል ዓይነቶችን ዘርዝሩ።

## መነጠል

በምሳሌው መሠረት የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡- ልብስዋ → ልብስ - ዋ

ልብሱ → ልብስ - ኡ

| | | |
|---|---|---|
| 1. እናትዋ | 3. ቀሚስዋ | 5. ደብተርሽ |
| 2. አባቱ | 4. እርሳሴ | 6. ቤቱ |

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. እነብርቱካን አቶ ይልማን ምን ብለው ጠየቋቸው?
2. ወላጆች ጠቃሚ ነገሮችን ለልጆቻቸው በምን መንገድ ያስተምራሉ?
3. የአካባቢያቸውን ባሕል የማይከተሉ ሰዎች ምን ችግር ይገጥማቸዋል?
4. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአራት ዓረፍተነገሮች ባጭሩ ግለጹ፡፡

### ቃላት

በ“ሀ” ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ”ሥር ከተዘረዘሩት ፍቺዎች ጋር አዛምዱ፡፡

| | “ሀ” | | “ለ” |
|---|---|---|---|
| 1. | ባህል | ሀ. | ከኑሮ ጓደኛ ጋር መቆራኘት |
| 2. | ጋብቻ | ለ. | የዕድሜ እኩያ |
| 3. | አቻ | ሐ. | ለረጅም ጊዜ የተካበተ ልምድ |
| 4. | ልደት | መ. | የተወለዱበት ቀን |

### መጻፍ

የቃላትን ቅደምተከተል በማስተካከል ተገቢውን ሥርዓተነጥቦች ተጠቅማችሁ ዐረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ፡፡

ምሣሌ፡- ዘወትር ታታሪዋ ታጠናለች ተማሪ

ታታሪዋ ተማሪ ዘወትር ታጠናለች፡፡

1. በሩጫ ወጣት አሸነፈች ጠይሟ
2. ሰው የማይጨናነቅ ይደሰታል ሁልጊዜ
3. እየሮጠ መጣ ልጅ ጥቁሩ
4. ተማሪ የቀይዳማዋ ታጠናለች ዘወትር
5. ውሻ አዳኙ መጣ እየሮጠ

26ኛ ሣምንት

## ግለንባብ

### ጠቃሚ ልማዶቻችን



በአካባቢያችሁ ስላሉ ጠቃሚ ልማዶች ምን ታውቃላችሁ? ከአካባቢያዊ ጠቃሚ ልማዶች መካከል በመቻቻል አብሮ መኖር፣ ልዩነትን መቀበል፣ የተጣላን ማስታረቅ፣ መጋባት፣ መውለድና ተንከባክቦ ማሣደግ የመሳሰሉትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል:: በመሆኑም አካባቢያዊ ጠቃሚ ልማዶችን አውቆና አክብሮ መሥራት ይጠቅማል::

የአመለካከት ልዩነቶች በሰዎች መካከል እንዳሉ ይታወቃል:: እነዚህን ልዩነቶች ተቀብሎ በመቻቻል አብሮ መሥራት ተገቢ ነው:: የአመለካከት ልዩነት አብሮ ለመሥራትና አብሮ ለመኖር አያግድም:: እንዲሁም አብሮ በመኖርና አብሮ በመሥራት ሂደት ውስጥ የሃሳብ ልዩነት ሊፈጠር ይችላል:: የሀሳብ ልዩነቱ ወደጠብ የሚያመራበት አጋጣሚም አለ:: በዚህ ጊዜ የተጣሉ ወገኖችን በማስታረቅ ግጭቱን ማስወገድ ይገባል::

መጋባትና መውለድም ሌላው አካባቢያዊ ጠቃሚ ልማድ ነው:: ጠቃሚ ልማድ መሆን የሚችለው ግን ሁለቱ ተጋቢዎች ማለትም ሴቷ ወይም ወንዱ ዕድሜያቸው ደርሶ በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ጋብቻ ሲፈጽሙና ጋብቻው ፀንቶ ሲኖር ነው::

ባጠቃላይ በሰዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ መቻቻል፣ ልዩነትን ተቀብሎ በሰላም አብሮ መኖር፣ የተጣላን ማስታረቅና በጋብቻ ፀንቶ መኖር ጠቃሚ ልማዶች መሆናቸውን በቤተሰብ፣ በአካባቢና በትምህርትቤት ለልጆች ማስገንዘብና ማስተማር ያስፈልጋል::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



ተሸላሚዋ ወይዘሮ

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት በቡድን ተወያይታችሁ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መቻቻል | መረዳዳት | ማፅናናት | ማስገንዘብ |

### ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ቅጥያዎች አጣምሩ።

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | ቅጥያዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | -ኡ | -ዋ | -ህ | -ሽ | -ኣችሁ |
| 1 | ቤት | ቤቱ | ቤትዋ | ቤትህ | ቤትሽ | ቤታችሁ |
| 2 | ልብስ | | | | | |
| 3 | እህት | | | | | |
| 4 | ወንድም | | | | | |
| 5 | ልጅ | | | | | |
| 6 | አገር | | | | | |

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. ለአብነት የተጠቀሱትን ልዩ ልዩ ልምዶች ዘርዝሩ።
2. አብሮ በመኖርና አብሮ በመሥራት ሂደት ውስጥ ምን ሊፈጠር ይችላል?
3. ልማዶችን ጠቃሚ የምንላቸው ምን ሲሆኑ ነው?
4. የመጀመሪያውን አንቀጽ ዋናሃሳብ የያዘው ዐረፍተነገር የትኛው ነው?

## ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማስታረቅ | ልዩነትን መቀበል | ማስታረቅ | መጋባት |

1. ለጋብቻ ዕድሜ ሲደርስ ____________ ጥሩ ባህል ነው?
2. የተጣሉ ሰዎችን ____________ ተገቢ ነው።
3. በትንሹም በትልቁም ነገር ሳይጋጩ በ ____________መኖር ይጠቅማል።
4. ልዩነታችን ውበታችን መሆኑን በመረዳት ____________ ያስፈልጋል።

## መጻፍ

የምንባቡን ማጠቃለያ በራሳችሁ አባባል ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ጽሁፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ተሸላሚዋ ወይዘሮ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. ወይዘሮ ታደለችን ተሸላሚ ለመሆን ያበቃት ማን ነው?
2. ከምንባቡ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ።

## መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ዋናቃላቸውንና ቅጥያቸውን ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡- ቤቷ → ቤት - ዋ

ቤትህ → ቤት - ህ

1. መጽሐፏ
2. እርሳስሽ
3. ቦርሳህ
4. ደብተሯ
5. እናቱ
6. አክስቴ

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

1. ተማሪዎች መማር ያለባቸው ጠቃሚ ልማዶች ምን ምን ናቸው?
2. ሰዎች አብረው እንዳይኖሩና እንዳይሠሩ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድን ነው?
3. ጋብቻ ጠቃሚ ልማድ ሊሆን የሚችለው ምን ሲሆን ነው?
4. የምንባቡን ማጠቃለያ ሃሳብ በራሳችሁ አባባል በሁለት ዓረፍተነገሮች ባጭሩ ግለጹ።

## ቃላት

በ"ሀ"ሥር ያሉትን ቃላት በ"ለ" ሥር ካሉት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1. | መቻቻል | ሀ. | ማስማማት |
| 2. | ማስታረቅ | ለ. | መከባበር |
| 3. | መፈቃቀድ | ሐ. | መተሳሰብ |
| 4. | ማስገንዘብ | መ. | ማሣወቅ |

## መጻፍ

"ጎጂ ልማዶች" በሚል ርዕስ ከ5-10 በሚደርሱ ዓረፍተነገሮች አንድ አንቀጽ ጻፉ። የጻፋችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ግለንባብ

### ውይይት የፈታው ችግር



አቶ አስናቀ የሚኖሩበት አካባቢ በልማት ደካማ ነው:: ማህበረሰቡ የመብራት፣ የመንገድና የቧንቧ ውሃ ተጠቃሚ አይደለም:: ለዚህ ምክንያቱ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ጎጂ ልማድ እንደሆነ ይነገራል:: አቶ አስናቀ የልማት ኮሚቴ አስተባባሪ ናቸው:: የልማት ኮሚቴውን ሰብስበው “በአካባቢው ያሉትን ጎጂ ልማዶች ለይተን እንወቅ” በሚል ርዕስ ተወያዩ:: ከኮሚቴ አባላት አንዷ ሶስና ትባላለች:: ሶስና የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያ ናት:: ሶስና “ጎጂ ልማዶቹ በጥናት ተለይተው ይታወቃሉ:: በአካባቢው ከሚዘወተሩት ዋና ዋናዎቹ ከአቅም በላይ ድግሥ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ብቀላና የጾታ መድሎ ናቸው፤ መፍትሔውም ማህበረሰቡን በማስተማር ማሣመን” እንደሆነ ገለፀች::

★★★“ህብረተሰቡን እንዴት ማስተማር ይቻላል ብላችሁ ታስባላችሁ?”★★★

ኮሚቴው ከዚህ በመነሳት በዕድር፣ በወጣት ማህበር፣ በእምነት ቦታዎች ማህበረሰቡን የማስተማርና የማሳመን ሥራዎች እንዲሠሩ አደረገ:: ቀስበቀስም ከአቅም በላይ በመደገስ ሀብት ማባከኑ እየቀነሰ መጣ:: በሰዎች መካከል ግጭት ሲፈጠር ቶሎ በሽምግልና የሚፈታበት ሥርዓት ተመቻቸ:: በጾታ መድሎና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጫናዎች ተቃለሉ:: ማህበረሰቡ ፊቱን ወደልማት አዞረ:: ሴቱም ወንዱም በአካባቢ ጥበቃ፣ በመስኖና በመሠረተ ልማት የሚያደርገው ተሳትፎ ጨመረ:: ማህበረሰቡ ጎጂ ልማዶቹ የልማቱና የዕድገቱ መሰናክል እንደሆኑ ተገነዘበ:: በተለይም ሴቶች በልማት ተሳትፏቸው ጠንካራ መሆናቸው ተረጋገጠ::

በልማት ኮሚቴው ጥረት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በመቀነሳቸውና ማህበረሰቡ ልማቱን በማፋጠኑ ኑሮው ተቀየረ:: ተሳስቦና ተፋቅሮ መኖር ቀጠለ:: ፍላጎቱ ተሟላ፤ ጤንነቱ ተጠበቀ::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



### ጎጂ ልማዶች

### ቃላት

በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ፍቻቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ያላቻ ጋቻ | ሀ. ለአካለመጠን ሳይደርሱ መዳር |
| 2. ግግ ማውጣት | ለ. ግግ መፈልፈል |
| 3. ያለዕድሜ ጋብቻ | ሐ. በዕድሜ ያልተመጣጠነ ጋብቻ |

### መነጠል

በቡድን ተደራጁ። አንድ ቡድን ባለቅጥያ ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን ዋናውን ቃልና ቅጥያን ይነጥላል። ዋና ቃልና ቅጥያውን የነጠለው ቡድን በተራው ባለቅጥያ ቃል ሲጠራ ሌላው ቡድን ዋናውን ቃልና ቅጥያን ይነጥላል። በዚህ መንገድ ጨዋታው ይቀጥላል።

ምሳሌ፡- ቡድን "ሀ" ቡድን "ለ"

ቤትዋ → ቤት - ዋ

ቤት - ኡ - ← ቤቱ

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ።

1. ጎጂ ልማዶች በመቀረፋቸው ምን ለውጥ መጣ?
2. በምንባቡ ውስጥ በችግርነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል ጨርሱት።

## ቃላት

በ"ሀ" ምድብ የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ምድብ ከሚገኙት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዷቸው።

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1. | ተጠቃሚ | ሀ. | የችግር ማቃለያ |
| 2. | ኮሚቴ | ለ. | የሰዎች ስብስብ |
| 3. | መፍትሔ | ሐ. | የሚፈልገውን ነገር የሚያገኝ |
| 4. | ማሳመን | መ. | ማግባባት |

## መጻፍ

"ትምህርትቤቴ" በሚል ርዕስ ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች አንድ አንቀጽ ጻፉ። በጽሁፉ ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ጎጂ ልማዶች

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

1. በምሳሌነት የተጠቀሱት ጎጂ ልማዶች ምን ምን ናቸው?
2. የሴት ልጅ ግርዛት ምን ምን ችግሮችን የሚያመጣ ይመስላችኋል?
3. ጎጂ ልማዶችን ለማስቀረት የእናንተ ድርሻ ምንድን ነው?

## ማጣመር

ከራሳችሁ ቃል በመፈለግ "-ኡ፣ -ዋ፣ -ህ፣ -ሽ" ከሚሉት ቅጥያዎች ጋር በምሳሌው መሠረት በማጣመር ባለቅጥያ ቃል መሥርቱ ።

ምሳሌ፡- ቤት → ቤቷ　　　　እርሳስ → እርሳስህ

ፀጉር → ፀጉሩ　　　　ቦርሳ → ቦርሳሽ

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

1. በእነሶስና አካባቢ በጥናት የተለዩ ጎጂ ልማዶች ምን ምን ናቸው?
2. ጎጂ ልማዶችን እንዴት ማስቀረት ይቻላል?
3. የምንባቡን ዋና ሃሳብ (መልእክት) ባጭሩ ግለጹ።

## ቃላት

በ"ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1. | መቧጠጥ | ሀ. | ግብዣ |
| 2. | የፆታ መድሎ | ለ. | የፆታ እኩልነት አለመኖር |
| 3. | ብቀላ | ሐ. | ቂም መወጣት |
| 4. | ድግስ | መ. | መቧጨር |

## መጻፍ


"ውይይት የፈታው ችግር" በሚል ርዕስ የተጻፈውን ምንባብ በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ ጻፉ።

# 28ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ምርቶቻችን

የተለያዩ ምርቶች ለገበያ ይቀርባሉ። ጥቂቶቹን መጥቀስ ቢያስፈልግ አልባሳት፣ እህል፣ እንስሳት፣ ቅመማቅመም፣ ምግብና መጠጥ ናቸው። እነዚህ ምርቶች ከአርሶአደሮች በቀጥታ የሚመጡ ሲሆኑ ሌሎቹ የፋብሪካ ውጤቶች ናቸው።



ከምርቶቻችን መካከል ወደውጭ የሚላኩም አሉ። ለምሳሌ ከአልባሳት ምርቶቻችን መካከል የቆዳና የሸመና ልብሶች ዋንኛ ተጠቃሽ ናቸው። የምርቶቹ ጥራት በተጠበቀ ቁጥር በገበያ ላይ ያላቸው ተወዳዳሪነት ይጨምራል።

የምግብና የመጠጥ ምርቶቻችን ለሀገር ውስጥ ገበያ ይውላሉ። ተጠቃሚው ብዙ ነው። ስለሆነም አልፎ አልፎ እጥረት ይታያል። እጥረቱን ለመሸፈን የፋብሪካዎቹ አቅምና ቁጥር መጨመር አለበት። ይህ ሲሆን ፍላጎትና አቅርቦት ይጣጣማሉ። የፓስታ፣ መኮረኒ፣ ዳቦና ስኳር ምርቶች አሁን ካሉበት የበለጠ እንዲጨምሩ ይፈለጋል። እነዚህ ምርቶች ከመሠረታዊ ፍላጎቶቻችን ውስጥ ይካተታሉ። ለአመጋገብ ሥርዓታችን መለወጥም አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ምርቶቹ በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠርም በስፋት እንዲለመዱ ይፈለጋል።

ከምርቶቻችን ጋር በተያያዘ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ አለ። ይህም ምርቶቻችን በህገወጥ መንገድ ወደውጭ እንዳይወጡ የመከላከል ሥራ ነው። ለምሳሌ የቀንድ ከብቶቻችን በህገወጥ መንገድ ወደውጭ እየወጡ ይሸጣሉ። ይህ የሀገርን ምጣኔ ሀብት ይጎዳል። በመሆኑም ለዚህ ህገወጥ አሠራር በር መከፈት የለበትም።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ልጆች ልብስ ተገዛላቸው**



### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በቡድን በመወያየት ዐረፍተነገሮችን ሥሩ::

| | | |
|---|---|---|
| 1. ጉልት | 3. በዓይነት | 5. ሸቀጥ |
| 2. መደበኛ ገበያ | 4. የገንዘብ | 6. ሱቅ በደረቴ |

ምሳሌ፡- ጥንት በገንዘብ ሣይሆን <u>በዓይነት</u> ልውውጥ ግብይት ይካሄድ ነበር::

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ::

ምሳሌ፡- ኮትህ → ኮት - ህ

ልብስሽ → ልብስ - ሽ

እርሳሱ → እርሳስ - ኡ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ጫማዋ | 3. መጽሐፉ | 5. ዘመዱ |
| 2. ልጁ | 4. ጓደኛዋ | 6. መምህሩ |

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ለገበያ ከሚቀርቡ ምርቶች ሶስቱን ጥቀሱ?
2. ምርቶች የምን የምን ውጤቶች ናቸው?
3. ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማጣጣም ምን ሊደረግ ይገባል?
4. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ ሀሳብ ባጭሩ ግለጹ፡፡

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ” ሥር ከሚገኙት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | “ሀ” | | “ለ” |
|---|---|---|---|
| 1. | ምርት | ሀ. | ማስማማት |
| 2. | አልባሳት | ለ. | ከጥጥ፣ ከቆዳ ወዘተ. የሚሠሩ ልብሶች |
| 3. | ፈትል ልብሶች | ሐ. | የፋብሪካ ወይም የግብርና ውጤት |
| 4. | ጥራት | መ. | ከጥጥ የሚሠሩ ልብሶች |
| 5. | ማጣጣም | ሠ. | እንከንየለሽ |

## መጻፍ

“አርሶአደር ብሆን ማምረት የምፈልጋቸው የምርት ዓይነቶች” በሚል ርዕስ ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ በዐረፍተነገሮቹ ውስጥም ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ልጆች ልብስ ተገዛላቸው**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ልጆቹ በአዲሱ ልብስ በመደሰታቸው ምን አደረጉ?
2. እነወይዘሮ ብርቱካን ምን በማለት ቃል ገቡ?
3. ልጆቹ ከጨዋታ ሲመለሱ ወላጆቻቸው ምን አሏቸው?
4. የምንባቡን መልዕክት በሶስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ፡፡

### ማጣመር

**(-ኤ፣-ኣችን፣ -ህ፣ -ሽ፣ -ኡ፣ -ዋ) የሚሉትን ቅጥያዎች በመጨመር በምሣሌው መሠረት ባለቅጥያ ቃላትን መስርቱ፡፡**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምሣሌ፡- | ልብስ | → | ልብሴ | ቀሚስ | → | ቀሚስሽ |
| | እናት | → | እናታችን | ደብተር | → | ደብተሩ |
| | ኮት | → | ኮትህ | ጫማ | → | ጫማዋ |

## 4ኛ ቀን

### ግለንባብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ወደውጭ ከሚላኩ ምርቶች በምሳሌነት የቀረቡት ምን ምን ናቸው?
2. የምርትን ጥራት መጠበቅ ጥቅሙ ምንድን ነው?
3. ከምርቶች ጋር በተያያዘ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ተግባር ምንድን ነው?
4. የምንባቡን ማጠቃለያ በራሳችሁ አባባል ባጭሩ ግለጹ?

## ቃላት

በቡድን ሆናችሁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በቁርጥራጭ ወረቀቶች ጻፉ። ወረቀቶችን በዕጣ መልክ ጠቅልሏቸው። ተራበተራ እጣውን አውጡ። ባወጣችሁት ዕጣ ላይ የተጻፈውን ቃል ካነበባችሁ በኋላ ዐረፍተነገር ሥሩበት። ለሁሉም ተማሪዎች እስኪዳረስ ጨዋታው ይቀጥል። አንድ ጊዜ የተሠራ ዐረፍተነገር አይደገምም።

1. አልባሳት
2. እህል
3. እንስሳት
4. ቅመማቅመም
5. መጠጥ
6. ምግብ


## መጻፍ

በአካባቢያችሁ ያለውን መደበኛ ገበያ በመጎብኘት የተመለከታችሁትን ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

# ግለንባብ

## ዕርቀሰላም ወረደ

ወይዘሮ አስካለና ወይዘሮ ዘውዱ ጎረቤታሞች ናቸው:: አልፎአልፎ ይጋጫሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የላለ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን የወይዘሮ አስካለ ልጅ ሮማን ታማ ሀኪምቤት ተኛች::



የወይዘሮ ዘውዱ ልጅ ርብቃ የክፍል ጓደኛዋን ልትጠይቃት ወደሀኪም ቤት ሄደች:: ርብቃ የታመመችውን የክፍል ጓደኛዋን ስታይ አለቀሰች:: እቤቷ ስትደርስ "ዘውድዬ ሮማንን ዛሬ ሀኪምቤት ሄጄ ጠየቅኋት:: አጠገቧ ያሉ ታማሚዎች ብዙ ጠያቂ አላቸው:: ብዙ የሚበላ ነገርም ይወስዱላቸዋል:: እርሷ ግን ብዙም ጠያቂ የላትም:: አጥሚት አዘጋጅተን አንቺ፣ አባባና እኔ ብንጠይቃት?" አለቻቸው:: ወይዘሮ ዘውዱ ብዙ ካሰቡ በኋላ "እስኪ እንዳልሽው ይሁን:: ነገ ሄደን እንጠይቃታለን" ሲሏት እቅፍ አርጋ ሳመቻቸው:: በሚቀጥለው ቀን አመሻሽ ላይ ወይዘሮ ዘውዱ አጥሚት አዘጋጅተውና እንጀራ ፈትፍተው ታማሚዋን ጠየቋት::

✶✶✶"የርብቃ ወላጆች ሮማንን በመጠየቃቸው ወላጆቿ ምን የሚሰማቸው ይመስላችኋል?"✶✶✶

የሮማን እናትና አባት የርብቃ ወላጆች ቅሬታቸውን በመተው ልጃቸውን ለመጠየቅ በመምጣታቸው ተደነቁ:: ሮማን ድና ወደቤቷ ተመለሰች:: ሁሉም ጎረቤታሞች ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግንኙነታቸው ተጠናከረ:: በጥሩ መንፈስ ሰላምታ ይለዋወጣሉ:: በርብቃ በጎ አመለካከት በመካከላቸው የነበረው አለመግባባት ተፈታ፤ ዕርቀሰላም ወረደ::

ሮማን ዛሬ በጋዜጠኝነት ሙያ ተሠማርታ ትሠራለች:: በልጃቸው ድጋፍ የወላጆቿ ኑሮ ተሻሽሏል:: የርብቃን ቤተሰቦች እንደራሷ ቤተሰብ ትወዳቸዋለች:: ለሥራ ከቦታ ቦታ ስትንቀሳቀስ ጥሩ ጥሩ የባህል ዕቃዎችን እያመጣች ትሰጣቸዋለች::

# 1ኛ ቀን



## ማዳመጥ

ገበያና ጥቅሙ

## ቃላት

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- <u>አቅርቦት</u> → በሚፈለገው መጠን ማሟላት

1. ፍላጎት
2. ትርፍ
3. ግብይት
4. የዓይነት ልውውጥ
5. የጎላ
6. ገበያ

## ማጣመር

የሚከተሉትን ዋና ቃላትንና ቅጥያዎችን በማጣመር ባለቅጥያ ቃላትን መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | ቅጥያ | ቃል |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንድም | -ኤ<br>-ህ<br>-ሽ<br>-ኡ<br>-ዋ | ወንድሜ |
| 2 | ዛፍ | | |
| 3 | ድመት | | |
| 4 | ውሻ | | |
| 5 | አባት | | |
| 6 | ቦርሳ | | |
| 7 | መምህር | | |

# 2ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የወይዘሮ አስካለች ልጅ ምን ሆነች?
2. በሰዎች መካከል ግጭት ሲፈጠር በአካባቢያችሁ ምን ይደረጋል?
3. የምንባቡን መልዕክት በአራት ዓረፍተነገሮች ግለጹ፡፡

## ቃላት

በ"ሀ" ሥር ያሉትን ቃላት በ"ለ" ሥር ካሉት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1. | መታመም | ሀ. | መጥላት |
| 2. | አመሻሽ | ለ. | ረፋድ |
| 3. | እርቀሰላም | ሐ. | ጠብ |
| 4. | መውደድ | መ. | ኪሣራ |
| 5. | ትርፍ | ሠ. | መዳን |

## መጻፍ

የሰፈራችሁ ነዋሪዎች ከገበያ ምን ምን ነገሮችን እንደሚገዙ ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች ግለጹ። በዐረፍተነገሮቹ ውስጥም ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ገበያና ጥቅሙ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የዕቃዎች ዋጋ የሚጨምረው በምን ምክንያት ነው?
2. የምርት ዋጋ እንዴት ይተመናል?
3. ከማዳመጥ ምንባቡ የተገነዘባችሁትን በሶስት ዓረፍተነገሮች ገለጹ።

## መነጠል

በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት የስም ገላጭ፣ ስም፣ የግሥ ገላጭና ግሥ በማለት በምሳሌው መሠረት ሥሩ::

| ተ.ቁ | ዓረፍተነገር | የስም ገላጭ | ስም | የግሥ ገላጭ | ግሥ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ረጅሟ ልጅ በሩጫ አሸነፈች:: | ረጅሟ | ልጅ | በሩጫ | አሸነፈች |
| 2 | ወፈራሙ ዛፍ ትናንት ተቆረጠ:: | | | | |
| 3 | አዲሱን ቀሚስ ዛሬ ለበሰችው:: | | | | |
| 4 | ጎበዙ ልጅ ዘወትር ያጠናል:: | | | | |
| 5 | ወይኒቱ በጣም ታምራለች:: | | | | |

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ::

1. የወይዘሮ ዘውዴ ልጅ ወዴት ሄደች?
2. የሮማን እናትና አባት በምን ተደሰቱ?
3. የምንባቡን ዋና ሃሳብ በአንድ አንቀጽ ግለጹ::

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት አጫጭር ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

1. አቅርቦት 2. ፍላጎት 3. ትርፍ 4. ግብይት

## መጻፍ

በአካባቢያችሁ ያሉ ነጋዴዎች ለሸማቾች የሚሸጧቸውን ነገሮች ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዓረፍተነገሮች ግለጹ::

በጽሁፋችሁ ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን አስገቡ::

## ግለንባብ

### የግብይት ሥርዓት



በግብይት ሂደት ውስጥ ሁለት ጎልተው የሚታዩ ተዋንያን አሉ:: የመጀመሪያዎቹ አቅራቢ የሆኑት ነጋዴዎች ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ተጠቃሚ የሆኑት ሸማቾች ናቸው:: ሸማች ማን ነው? ሸማች ከአምራቹ ወይም ከነጋዴው ገዝቶ የሚጠቀም ነው:: አፈጻጸሙም የሚፈልገውን ነገር ከአቅራቢው መጠየቅ፣ ዋጋ እንዲቀንስለት መከራከር፣ ሲስማማው መግዛትና በመጨረሻ ክፍያውን ፈፅሞ ምርቱን ወይም የተገዛውን ነገር መቀበል ነው::

የሸማች ተግባር ባጭሩ ይህን ቢመስልም ፍላጎትና አቅርቦት ባልተመጣጠኑበት የግብይት ሥርዓቱ ውጣውረድ ብዙ ነው:: አንደኛ ከቦታ ቦታ የምርቱ ዋጋ ይለያያል:: ጥራቱም እንዲሁ ልዩነት አለው:: አንዳንዴ ደግሞ ሸማቹ የያዘው ገንዘብ ከሚጠራው የምርት ዋጋ በማነሱ ይቸገራል:: እንዲሁም የተገዛው ምርት የተበላሸ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ:: ለምሣሌ፣ የተሸመተው ጤፍ እንጀራው ላያምር ይችላል:: ቅቤውና ማሩም ከማይፈለግ ባዕድ ነገር ጋር የተደባለቀ ሆኖ ሲገኝ ሊጣል ይችላል::

ስለዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የሸማቾች ችግር ለማቃለል ለምርት ዓይነቶቹ የመሸጫ ቦታ ቢመደብ፣ ለእያንዳንዱ ምርት የመሸጫ ዋጋ ቢለጠፍ፣ የምርቱን ጥራት ማረጋገጫ ዘዴ ቢፈጠርና የሸማቹ ደህንነት የሚጠበቅበት ሁኔታ ቢመቻች የተሻለ የግብይት ሥርዓት ይፈጠራል::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ






ነጋዴዋ ሉባባ

### ቃላት

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጻፉ።

1. አቅርቦት 2. መሸጥ 3. በዓይነት 4. መከፋፈል 5. መቸርቸር

### ማጣመር

የሚከተሉትን ዋና ቃላትና ቅጥያቸውን በማጣመር ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ።

| ተ.ቁ | ዋና ቃል | -ዋ | -ሉ | -ህ | -ሽ | -ኦች | -ዎች | -ኣት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንበር | ወንበሯ | ወንበሩ | ወንበርህ | ወንበርሽ | ወንበሮች | - | - |
| 2 | እርሳስ | | | | | | | |
| 3 | ህጻን | | | | | | | |
| 4 | ደብተር | | | | | | | |
| 5 | አገር | | | | | | | |
| 6 | ጫማ | | | | | | | |
| 7 | ቦርሳ | | | | | | | |

## 2ኛ ቀን

### ግለንባብ

የሚከተሉትን ቅጥያዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

1. በግብይት ወቅት ጎልተው የሚታዩት ሁለቱ ተዋንያን እነማን ናቸው?
2. የግብይት ሥርዓቱ ውጣውረድ የሚበዛበት ምን ሲኖር ነው?
3. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

## ቃላት

በምሳሌው መሠረት የስም ገላጮችን፣ ስሞችን፣ የግስ ገላጮችንና ግሶችን በቅደምተከተል አስተካክላችሁ ጻፉ::

ምሳሌ:- ወጣቱ በጣም ልጅ ያምራል::

ወጣቱ ልጅ በጣም ያምራል::

1. አሸነፈ ሰውዬ ፈጣኑ በሩጫ::
2. ዛሬ ጎበዙ ተሸለመ አርሶአደር::
3. ወጣች አንደኛ ተማሪ ጎበዟ በፈተና::
4. መጣች ጠይሟ ዛሬ አስተማሪ::

## መጻፍ

“ነጋዴ ብሆን” በሚል ርዕስ ከአምስት እስከአሥር በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች አንድ አንቀጽ ጻፉ:: በጽሁፉ ውስጥ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን ተጠቀሙ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ነጋዴዋ ሉባባ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ::

1. አቶ የሱፍ ደስተኛ ያልሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ሉባባ ለቤተሰቦቿ ምን አደረገች?
3. ሉባባ ምን በመሥራቷ ለሌሎች አርአያ ሆነች?
4. የምንባቡን መልዕክት በሶስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ::

## ማጣመር

በራሳችሁ ቃል በመፈለግ (-ኤ፣-ህ፣-ሽ፣-ኡ፣-ዋ) የሚሉትን ቅጥያዎች በማጣመር በምሳሌው መሠረት ባለቅጥያ ቃል መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- እግር → እግሬ  ፀጉር → ፀጉርሽ  ቦርሳ → ቦርሳዋ

እጅ → እጅህ  ሸሚዝ → ሸሚዙ

# 4ኛ ቀን

## ግለንባብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. አንዳንድ ጊዜ ሸማቾች የሚቸገሩት ምን ሲኖር ነው?
2. ሸማቾች ከነጋዴው ሣይሆን ከአርሶአደሩ ለመግዛት የሚገደዱት ምን ሲኖር ነው?
3. የምንባቡን ሀሳብ ባጭሩ ግለፁ፡፡

## ቃላት

በ“ሀ” ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ“ለ” ሥር ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. መሸጥ | ሀ. የዋጋ ቅናሽ እንዲደረግ መደራደር |
| 2. መለወጥ | ለ. እያንዳንዱን የዕቃ ዓይነት በተናጠል መሸጥ |
| 3. ማከፋፈል | ሐ. ለተገዛ ዕቃ ዋጋ መስጠት |
| 4. መቸርቸር | መ. ማሠራጨት |
| 5. መከራከር | ሠ. ዕቃን በዕቃ መቀየር |
| 6. መክፈል | ረ. ገንዘብ በመቀበል ዕቃ መስጠት |

## መጻፍ

“የግብይት ስርዐት” የሚለውን ምንባብ ከሶስት እስከአምስት በሚደርሱ ዐረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡